IslamHouse.com
مركز أصول
Osoul Center
www.osoulcenter.com
Rabwah

# አል-ኡሱል አስ-ሰላሰህ

# ሶስቱ መሰረታዊ መርሆዎች

አዘጋጅ
ሙሐመድ ቢን ዐብዱልወሀብ
ትርጉም
ጋሊ አባቦር አባጉማ
እርማት
ሼኽ ጀማል ሼኽ ሙሐመድ

Amharic
አማርኛ
أمهري

# الأصول الثلاثة وأدلتها
# وشروط الصلاة

مركز أصول
ترجمة
الداعية غالي أبابور

مراجعة

الداعية جمال محمد أحمد

Amharic
አማርኛ
أمهري

ⓒ **جمعية الدعوة والإرشاد وتوعية الجاليات بالربوة، ١٤٤٢هـ**

**فهرسة مكتبة الملك فهد الوطنية أثناء النشر**

مركز أصول

الأصول الثلاثة وأدلتها وشروط الصلاة – اللغة الأمهرية. / مركز أصول؛ غالي ابابور - ط١.-

الرياض، ١٤٤٢هـ

٦٠ ص، ١٢ سم x ١٦,٥ سم

ردمك : ٠-٣٨-٨٣٢٣-٦٠٣-٩٧٨

١- العقيدة الإسلامية ٢- التوحيد أ. ابابور، غالي (مترجم)

ب. العنوان

**ديوي ٢٤٠** **١٤٤٢/٢٧١٦**

**رقم الايداع: ١٤٤٢/٢٧١٦**

**ردمك : ٠-٣٨-٨٣٢٣-٦٠٣-٩٧٨**

Osoul Center
www.osoulcenter.com

This book is the property of the Osoul Center. Permission is granted for it to be stored, transmitted, and published in any print, electronic, or other format - as long as the Osoul Center is clearly mentioned on all editions, no changes are made without the express permission of the Osoul Center, and a high level of quality is maintained.

+966 11 445 4900

+966 11 497 0126

P.O.BOX 29465 Riyadh 11457

osoul@rabwah.sa

www.osoulcenter.com




በአሏህ ስም እጅግ በጣም ርህሩህ
እጅግ በጣም አዛኝ በሆነው



አላህ ይዘንልህና አራት ጉዳዮችን መማር በኛ ላይ ግዴታ መሆኑን እወቅ:-

የመጀመርያው እውቀት ሲሆን እሱም በማስረጃ ላይ ተመስርቶ አላህን፣ መልእክተኛውንና የእስልምና ሐይማኖትን ማወቅ ነው፡፡

ሁለተኛው በእውቀቱ መስራት ነው፡፡

ሶስተኛው ወደሱ መጣራት ሲሆን

አራተኛው ደግሞ በደዕዋ ሂደት ላይ በሚያጋጥመው ችግሮች ላይ መታገስ ነው፡፡

የዚህ ማስረጃ የአላህ (ሱ.ወ) ቃል ነው:-

﴿وَٱلۡعَصۡرِ ١ إِنَّ ٱلۡإِنسَٰنَ لَفِي خُسۡرٍ ٢ إِلَّا ٱلَّذِينَ ءَامَنُواْ وَعَمِلُواْ ٱلصَّٰلِحَٰتِ وَتَوَاصَوۡاْ بِٱلۡحَقِّ وَتَوَاصَوۡاْ بِٱلصَّبۡرِ﴾ [العصر: ١-٣]

(በአላህ ስም እጅግ በጣም ሩህሩህ በጣም አዛኝ በሆነው፡፡ በጊዜያቱ እምላለሁ፡፡ ሰው ሁሉ በእርግጥ በከሳራ ውስጥ ነው፡፡ እነዚያ ያመኑትና መልካሞችን የሠሩት፣ በእውነትም አደራ የተባባሉት፣ በመታገስም አደራ የተባባሉት ብቻ ሲቀሩ፡፡) *[አል-ዐስር፡ 1-3]*

እማም አሽ-ሻፊዒ አላህ ይዘንላቸውና እንዲህ አሉ:- "አላህ በፍጡራኑ ላይ ከዚህ ምዕራፍ ሌላ ምንም ባያወርድ ኖሮ ትበቃቸው ነበረች፡፡"

እማም አልቡኻሪም አላህ ይዘንላቸውና እንዲህ አሉ፡- "ይህ ምእራፍ እውቀት ከመናገርና ከመስራት መቅደሙን ይገልፃል፡፡ ማስረጃውም የአላህ (ሱ.ወ) ቃል ነው፡-

﴿ فَٱعْلَمْ أَنَّهُۥ لَآ إِلَٰهَ إِلَّا ٱللَّهُ وَٱسْتَغْفِرْ لِذَنۢبِكَ ﴾ [محمد: ١٩]

(እነሆ ከአላህ ሌላ እውነት አምላክ አለመኖሩን ዕወቅ፡፡) *ሙሐመድ፡ 19*
ከንግግርና ከስራ በፊት በእውቀት ጀመረ፡፡"

አላህ ይዘንልህና እያንዳንዱ ሙስሊም ላይ እነዚህን ሶስት መሰረታዊ ጉዳዮችን መማርና በተግባር ላይ የማዋል ግዴታ እንዳለበት እወቅ፡-

01 አላህ ፈጠረንና ስሳዩን ሰጠን፤ እንዲሁም አልተወንም፡፡ ይልቁንስ መልእክተኛን ላከልን፡፡ እሱን የታዘዘ ሰው ጀነት ይገባል፡፡ እሱን ያመጸ ደግሞ ጀሀነም ይገባል፡፡ ማስረጃውም የአላህ (ሱወ) ቃል ነው፡-

﴿ إِنَّآ أَرْسَلْنَآ إِلَيْكُمْ رَسُولًا شَٰهِدًا عَلَيْكُمْ كَمَآ أَرْسَلْنَآ إِلَىٰ فِرْعَوْنَ رَسُولًا ﴿١٥﴾ فَعَصَىٰ فِرْعَوْنُ ٱلرَّسُولَ فَأَخَذْنَٰهُ أَخْذًا وَبِيلًا ﴾ [المزمل: ١٥-١٦]

"እኛ ወደ ፈርዖን መልክተኛን እንደላክን ሁሉ በእናንተ ላይ መስካሪ የሆነ መልእክተኛ ወደእናንተ ላክን፡፡ ፈርዖንም መልክተኛውን አመጸ፤ ብርቱ መያዝንም ያዝነው፡፡" *አልሙዘሚል፡ 15-16.*

02 አላህ (ሱ.ወ) በአምልኮቱ ዉስጥ አንድንም ነገር፤ ባለሟል መልዓከም ሆነ የተላከ ነቢይ በሱ ማጋራትን አይወድም፡፡ ማስረጃውም የአላህ (ሱ.ወ) ቃል ነው፡-

﴿ وَأَنَّ ٱلْمَسَٰجِدَ لِلَّهِ فَلَا تَدْعُوا۟ مَعَ ٱللَّهِ أَحَدًا ﴾ [الجن: ١٨]

እነሆ መስጅዶች ሁሉ የአላህ ናቸው፤ ከአላህ ጋር አንድንም አትገዙ፡፡ *አልጅን፡ 18*

03 መልእክተኛውን የታዘዘና የአላህን አንድነት ያረጋገጠ ሰው፣ አለህንና መልእክተኛውን የሚቃረንን ሰው በጣም የቅርብ ዘመዱም ቢሆንም እንኳ እንዲወዳቸው አይፈቀድለትም፡፡ ማስረጃውም ቀጣዩ የአላህ (ሱ.ወ) ቃል ነው፡-

﴿لَّا تَجِدُ قَوْمًا يُؤْمِنُونَ بِٱللَّهِ وَٱلْيَوْمِ ٱلْـَٔاخِرِ يُوَآدُّونَ مَنْ حَآدَّ ٱللَّهَ وَرَسُولَهُۥ وَلَوْ كَانُوٓا۟ ءَابَآءَهُمْ أَوْ أَبْنَآءَهُمْ أَوْ إِخْوَٰنَهُمْ أَوْ عَشِيرَتَهُمْ ۚ أُو۟لَـٰٓئِكَ كَتَبَ فِى قُلُوبِهِمُ ٱلْإِيمَـٰنَ وَأَيَّدَهُم بِرُوحٍ مِّنْهُ ۖ وَيُدْخِلُهُمْ جَنَّـٰتٍ تَجْرِى مِن تَحْتِهَا ٱلْأَنْهَـٰرُ خَـٰلِدِينَ فِيهَا ۚ رَضِىَ ٱللَّهُ عَنْهُمْ وَرَضُوا۟ عَنْهُ ۚ أُو۟لَـٰٓئِكَ حِزْبُ ٱللَّهِ ۚ أَلَآ إِنَّ حِزْبَ ٱللَّهِ هُمُ ٱلْمُفْلِحُونَ﴾ [المجادلة: ٢٢]

በአላህና በመጨረሻው ቀን የሚያምኑት ሕዝቦች አላህንና መልክተኛውን የሚከራከሩትን ሰዎች፤ አባቶቻቸው፣ ወይም ልጆቻቸው፣ ወይም ወንድሞቻቸው፣ ወይም ዘመዶቻቸው ቢኾኑም እንኳ የሚወዳጁ ኾነው አታገኛቸውም፡፡ እነዚያ በልቦቻቸው ውስጥ እምነትን ጽፏል፡፡ ከእርሱም በኾነ መንፈስ ደግፏቸዋል፡፡ ከሥሮቻቸውም ወንዞች የሚፈሱባቸውን ገነቶች በውስጣቸው ዘውታሪዎች ሲኾኑ ያገባቸዋል፡፡ አላህ ከእነርሱ ወዷል፡፡ ከእርሱም ወደዋል፡፡ እነዚያ የአላህ ሕዝቦች ናቸው፡፡ ንቁ! የአላህ ሕዝቦቸ እነርሱ ምኞታቸውን የሚያገኙ ናቸው፡፡ *አል-ሙጃደላህ፡ 22*

አላህ እሱን ለመታዘዝ ይቅናህና ቀጥተኛ የሆነው የኢብራሂም መንገድ

(ሐኒፍያ) የሚባለው ኀይማኖትን ለሱ ፍፁም በማድረግ አንድ አላህን ብቻ ማምለክ ነው፡፡አላህም ሰዎችን ሁሉ በሱ አዟል፤ ለዚህም አላማ ፈጠራቸው፡፡አላህ (ሱ.ወ) እንዲህ ይላል፡-

﴿وَمَا خَلَقْتُ ٱلْجِنَّ وَٱلْإِنسَ إِلَّا لِيَعْبُدُونِ﴾ [الذاريات: ٥٦]

ጋኔንንና ሰውንም ሊግገዙኝ እንጅ ለሌላ አልፈጠርኳቸውም፡፡ *አዝ-ዛርያት፡ 56*

ሊገዙኝ የሚለው ትርጉሙ እኔን በብቸኝነት እንዲያመልኩኝ ማለት ነው፡፡ ዋነኛው አላህ ያዘዘው ትእዛዝ ተውሒድ ሲሆን እሱም አላህን በብቸኝነት ማምለክ ነው፡፡ ትልቁ አላህ የከለከለ ነገር ሽርክ ሲሆን እሱም ከአላህ ጋር ሌላ ነገርን ማምለክ ነው፡፡ማስረጃውም ቀጣዩ የአላህ (ሱ.ወ) ቃል ነው፡-

﴿وَٱعْبُدُوا ٱللَّهَ وَلَا تُشْرِكُوا بِهِۦ شَيْـًٔا﴾ [النساء: ٣٦]

አላህን ብቻ ተገዙ፡፡ በእርሱም ምንንም አታጋሩ፡፡ *አን-ኒሳእ፡ 35*

“በሰዎች ላይ ማወቃቸው ግዴታ የሚሆኑት ሶስቱ መሰረታዊ መርሆዎች ምን ምን ናቸው?” ተብለህ ከተጠየክ የሚከተሉትን መልስ፡-

*አንድ ሙስሊም ጌታውን፣ ኀይማኖቱንና መልእክተኛው ሙሐመድን (ሰ.ዐ.ወ) ማወቅ ሶስቱ መርሆዎች ናቸው፡፡*

## የመጀመርያ መሰረታዊ መርህ

ባርያዉ ጌታውን ማወቅ

“ጌታህ ማነው?” ተብለህ ስትጠየቅ እንዲህ በማለት መልስ፡-

ጌታዬ እኔንና ዓለምን ሁሉ በፀጋው ያሳደገ አላህ ነው፤ እሱ አምላኬ ነው፤ ከሱ ዉጭ የማመልከ ነገር የለኝም፡፡ ማስረጃውም ቀጣዩ የአላህ (ሱ.ወ) ቃል ነው፡-

﴿ٱلۡحَمۡدُ لِلَّهِ رَبِّ ٱلۡعَٰلَمِينَ﴾ [الفاتحة : ٢]

“ምስጋና ለአላህ ለዓለማቱ ጌታ ይሁን” *አልፋቲሓ፡ 2*

ከአላህ ውጭ ያለው ሁሉ ፍጥረተ ዓለም ሲሆን እኔም ከዚህ ዓለም አንዱ ነኝ፡፡

“ጌታህን በምን አወቅከ?” ተብለህ ስትጠየቅ “በተኣምራቱና በፍጥረታቱ ነው ያወኩት” በል፡፡ የሚከተሉት ከተኣምራቶቹ ይመደባሉ፡- ሌሊት፣ ቀን፣ ፀሐይና ጨረቃ ናቸው፡፡ በፍጥረተ-ዓለሙ ዉስጥ ደግሞ ሰባቱ ሰማያት፣ሰባቱ ምድሮች፣ በነሱ ዉስጥ ያሉት ነገራቶችና በመሀከላቸው ያለው ሁሉ ይገባሉ፡፡ ማስረጃውም ቀጣዩ የአላህ (ሱ.ወ) ቃል ነው፡-

﴿وَمِنۡ ءَايَٰتِهِ ٱلَّيۡلُ وَٱلنَّهَارُ وَٱلشَّمۡسُ وَٱلۡقَمَرُۚ لَا تَسۡجُدُواْ لِلشَّمۡسِ وَلَا لِلۡقَمَرِ وَٱسۡجُدُواْۤ لِلَّهِ ٱلَّذِي خَلَقَهُنَّ إِن كُنتُمۡ إِيَّاهُ تَعۡبُدُونَ﴾ [فصلت: ٣٧]

ሌሊትና ቀንም ፀሐይና ጨረቃም ከምልክቶቹ ናቸው፡፡ ለፀሐይና ለጨረቃ አትስገዱ፡፡ ለእዚያ ለፈጠራቸው አላህ ስገዱ፡፡ እርሱን ብቻ የምትግገዙ እንደ ኾናችሁ (ለሌላ አትስገዱ)፡፡ *ፉስለት፡ 37*

﴿إِنَّ رَبَّكُمُ ٱللَّهُ ٱلَّذِي خَلَقَ ٱلسَّمَٰوَٰتِ وَٱلۡأَرۡضَ فِي سِتَّةِ أَيَّامٖ ثُمَّ ٱسۡتَوَىٰ عَلَى ٱلۡعَرۡشِۖ يُغۡشِي ٱلَّيۡلَ ٱلنَّهَارَ يَطۡلُبُهُۥ حَثِيثٗا وَٱلشَّمۡسَ وَٱلۡقَمَرَ وَٱلنُّجُومَ مُسَخَّرَٰتِۭ بِأَمۡرِهِۦٓۗ أَلَا لَهُ ٱلۡخَلۡقُ وَٱلۡأَمۡرُۗ تَبَارَكَ ٱللَّهُ رَبُّ ٱلۡعَٰلَمِينَ﴾ [الأعراف: ٥٤]

ጌታችሁ ያ ሰማያትንና ምድርን በስድስት ቀኖች ውስጥ የፈጠረ አላህ

ነው፡፡ ከዚያም (ለሱ በሚገባ መልኩ) በዐርሹ ላይ ተደላደለ፡፡ (አላህ) ሌሊትን በቀን ፈጥኖ የሚፈልገው ሲኾን ይሸፍናል፡፡ ፀሐይንና ጨረቃንም ከዋክብትንም በትእዛዙ የተገሩ ሲኾኑ (ፈጠራቸው)፡፡ ንቁ! መፍጠርና ማዘዝ የእርሱ ብቻ ነው፡፡ የዓለማት ጌታ አላህ (ክብሩ) ላቀ፡፡ *አል-አዕራፍ፡ 54*

ሊመለክ የሚገባ ይህ ጌታ ብቻ ነው፤ ማስረጃውም ቀጣዩ የአላህ (ሱ.ወ) ቃል ነው፡

﴿يَٰٓأَيُّهَا ٱلنَّاسُ ٱعۡبُدُواْ رَبَّكُمُ ٱلَّذِي خَلَقَكُمۡ وَٱلَّذِينَ مِن قَبۡلِكُمۡ لَعَلَّكُمۡ تَتَّقُونَ ٢١ ٱلَّذِي
جَعَلَ لَكُمُ ٱلۡأَرۡضَ فِرَٰشٗا وَٱلسَّمَآءَ بِنَآءٗ وَأَنزَلَ مِنَ ٱلسَّمَآءِ مَآءٗ فَأَخۡرَجَ بِهِۦ مِنَ ٱلثَّمَرَٰتِ رِزۡقٗا
لَّكُمۡۖ فَلَا تَجۡعَلُواْ لِلَّهِ أَندَادٗا وَأَنتُمۡ تَعۡلَمُونَ﴾ [البقرة: ٢١-٢٢]

እናንተ ሰዎች ሆይ! የፈጠራችሁን እነዚያንም ከናንተ በፊት የነበሩትን (የፈጠረውን) ጌታችሁን ተገዙ፤ (ቅጣትን) ልትጠነቀቁ ይከጀላልና፡፡ (እርሱ) ያ ለናንተ ምድርን ምንጣፍ ሰማይንም ጣራ ያደረገ ነው፤ ከሰማይም (ከደመና) ውሃን ያወረደ በርሱም ከፍሬዎች ለናንተ ሲሳይን ያወጣ ነው፡፡ እናንተም (ፈጣሪነቱን) የምታውቁ ስትኾኑ ለአላህ ባላንጣዎችን አታድርጉ፡፡ *አል-በቀራ፡ 21-22*

ኢብን ከሲር አላህ ይዘንላቸውና እንዲህ አሉ፡- “እነዚህን ነገር የፈጠራቸው ጌታ ሊመለክም የሚገባው እሱ ብቻ ነው፡፡”

አላህ ያዘዛቸው የዒባዳ አይነቶች፡-

01 የኢስላም ማእዘናት

02 የኢማን ማእዘናት

03 ኢህሳን (ዒባዳን ማሳመር)

04 ዱዓእ (ፀሎት)

05 ፍራቻ

06 ተስፋ

07 መመካት

08 ከጀላ

09 ቅጣት መፍራት

10 መተናነስ

11 እውቀት ላይ የተመሰረተ ፍራቻ

12 በንስሀ መመለስ

13 እርዳታ መፈለግ

14 ጥበቃን መፈለግ

15 ፈጣኝ እርዳታን መለመን

16 እርድ ማቅረብ

17 ስለት መሳል

18 ከዚህ ዉጭ ያሉ የአምልኮት አይነቶች ሁሉ የአላህ ሐቅ ናቸው፡፡

ማስረጃውም ቀጣዩ የአላህ (ሱ.ወ) ቃል ነው፡-

﴿وَأَنَّ ٱلۡمَسَٰجِدَ لِلَّهِ فَلَا تَدۡعُواْ مَعَ ٱللَّهِ أَحَدٗا﴾ [الجن: ١٨]

እነሆ መስጊዶችም የአላህ ብቻ ናቸው፡፡ ከአላህ ጋር አንድንም አትገዙ፡፡ *አልጅን፡18*

ከነዚህ የዒባዳ አይነቶች ጥቂትንም እንኳ ለማንኛዉም ከአላህ ሌላ

ላለው አካል ያዋለ ሰዉ እርሱ በአላህ ላይ አጋሪ (ሙሽሪክ) ብሎም ከሀዲ (ካፍር) ነዉ:: ለዚህም ማስረጃ:-

﴿ وَمَن يَدْعُ مَعَ ٱللَّهِ إِلَـٰهًا ءَاخَرَ لَا بُرْهَـٰنَ لَهُۥ بِهِۦ فَإِنَّمَا حِسَابُهُۥ عِندَ رَبِّهِۦٓ ۚ إِنَّهُۥ لَا يُفْلِحُ ٱلْكَـٰفِرُونَ ﴾ [المؤمنون: ١١٧]

ከአላህም ጋር ሌላን አምላክ ለእርሱ በእርሱ ማስረጃ የሌለውን የሚገዛ ሰው ምርመራው እጌታው ዘንድ ብቻ ነው:: እነሆ ከሓዲዎች አይድኑም:: *አልሙእሚኑን: 117*

በሀዲስ እንደ ተላለፈዉ «ዱዓዕ የዒባዳ መቅኔ ነዉ»::

﴿ وَقَالَ رَبُّكُمُ ٱدْعُونِىٓ أَسْتَجِبْ لَكُمْ ۚ إِنَّ ٱلَّذِينَ يَسْتَكْبِرُونَ عَنْ عِبَادَتِى سَيَدْخُلُونَ جَهَنَّمَ دَاخِرِينَ ﴾ [غافر: ٦٠]

ጌታችሁም አለ «ለምኑኝ፤ እቀበላችኋለሁና:: እነዚያ እኔን ከመግገዛት የሚኮሩት ተዋራጆች ኾነው ገሀነምን በእርግጥ ይገባሉ:: *ጋፍር 60*

ኸዉፍ (ፍራቻ) ለአላህ ብቻ ሲለመሆኑ ማስረጃዉ:-

﴿ إِنَّمَا ذَٰلِكُمُ ٱلشَّيْطَـٰنُ يُخَوِّفُ أَوْلِيَآءَهُۥ فَلَا تَخَافُوهُمْ وَخَافُونِ إِن كُنتُم مُّؤْمِنِينَ ﴾ [آل عمران: ١٧٥]

እንዲህ የሚላችሁ ሰይጣን ብቻ ነው:: ወዳጆቹን ያስፈራራችኋል:: አትፍሩዋቸውም:: ምእምናንም እንደኾናችሁ ፍሩኝ:: *ኣሊ ኢምራን: 175*

ተስፋን መጣል በአላህ ላይ ሲለመሆኑ ማስረጃው:-

﴿ قُلْ إِنَّمَآ أَنَا۠ بَشَرٌ مِّثْلُكُمْ يُوحَىٰٓ إِلَىَّ أَنَّمَآ إِلَـٰهُكُمْ إِلَـٰهٌ وَٰحِدٌ ۖ فَمَن كَانَ يَرْجُوا۟ لِقَآءَ رَبِّهِۦ فَلْيَعْمَلْ عَمَلًا صَـٰلِحًا وَلَا يُشْرِكْ بِعِبَادَةِ رَبِّهِۦٓ أَحَدًۢا ﴾ [الكهف: ١١٠]

የጌታውንም መገናኘት የሚፈልግ ሰው፤ መልካም ሥራን ይሥራ፡፡ በጌታውም መገዛት አንድንም አያጋራ፡፡ *አልከህፍ፡110*

መመካት በአላህ ላይ ሲለመሆኑ ማስረጃው፡-

﴿وَعَلَى ٱللَّهِ فَتَوَكَّلُوٓاْ إِن كُنتُم مُّؤۡمِنِينَ﴾ [المائدة: ٢٣]

“ምእመናን እነደሆናችሁ በአላህ ላይ ተመኩ” *አልማኢዳ፡ 23*

﴿وَمَن يَتَوَكَّلۡ عَلَى ٱللَّهِ فَهُوَ حَسۡبُهُۥٓ﴾ [الطلاق: ٣]

በአላህም ላይ የሚመካ ሰው እርሱ በቂው ነው፡፡ *አጥ-ጠላቅ፡ 3*

ከጀላ፣ ቅጣት ፍራቻና መተናነስ ለአላህ ብቻ ሲለመሆኑ ማስረጃው፡-

﴿إِنَّهُمۡ كَانُواْ يُسَٰرِعُونَ فِي ٱلۡخَيۡرَٰتِ وَيَدۡعُونَنَا رَغَبٗا وَرَهَبٗاۖ وَكَانُواْ لَنَا خَٰشِعِينَ﴾ [الأنبياء: ٩٠]

“እነርሱ በበጎ ሥራዎች የሚቻኮሉ ከጃዮችና ፈሪዎች ኾነው የሚለምኑንም ነበሩ፡፡ ለእኛ ተዋራጆችም ነበሩ፡፡” *አል-አንቢያእ፡ 90*

የመተናነስ ማስረጃው የአላህ (ሱ.ወ) ቃል ነው፡- “አትተናሰስላቸው ለነ ብቻ ተዋረጁልኝ፡፡” *አልበቀራ፡ 150*

ንስሀ መግባት ለአላህ ብቻ ሲለመሁኑ ማስረጃው፡- “በመፀፀት ወደ ጌታችሁ ተመለሱ፣ ለርሱም ታዘዙ፡፡” *አዝ-ዙመር፡ 54*

እርዳታ የሚጠየቀውም ከአላህ ሲለመሆኑ ማስረጃው፡- “አንተን ብቻ እንግገዛለን፤ አንተንም ብቻ እርዳታን እንለምናለን፡፡” *አልፋቲሓ፡ 5*

በሐዲስ ዉስጥ ደግሞ “እርዳታን ሲትጠይቅ ከአላህ ብቻ ፈልግ”

ይላል፡፡ ጥበቃ የሚፈለገዉም ከአላህ ብቻ ሲለመሆኑ ማስረጃው፡- "በሰዎች ፈጣሪ እጠበቃለሁ"በል፡፡" *አን-ናስ፡1*

ፈጣኝ እርዳታም የሚጠየቀው ከአላህ ብቻ ሲለመሆኑ ማስረጃው የአላህ (ሱ.ወ) ቃል ነው፡- "ከጌታችሁ እርዳታን በፈለጋችሁ ጊዜ ለናንተ የተቀበላችሁን (አስታውሱ)፡፡" *አል-አንፋል፡ 9*

የሚታረደዉም ለአላህ ብቻ ሲለመሆኑ ማስረጃው የአላህ (ሱ.ወ) ቃል ነው፡-

﴿قُلْ إِنَّنِي هَدَىٰنِي رَبِّيٓ إِلَىٰ صِرَٰطٍ مُّسْتَقِيمٍ دِينًا قِيَمًا مِّلَّةَ إِبْرَٰهِيمَ حَنِيفًا ۚ وَمَا كَانَ مِنَ ٱلْمُشْرِكِينَ ﴿١٦١﴾ قُلْ إِنَّ صَلَاتِى وَنُسُكِى وَمَحْيَاىَ وَمَمَاتِى لِلَّهِ رَبِّ ٱلْعَٰلَمِينَ ﴿١٦٢﴾ لَا شَرِيكَ لَهُۥ ۖ وَبِذَٰلِكَ أُمِرْتُ وَأَنَا۠ أَوَّلُ ٱلْمُسْلِمِينَ﴾ [الأنعام: ١٦١-١٦٣]

"«እኔ ጌታዬ ወደ ቀጥተኛው መንገድ ትክክለኛን ሃይማኖት ወደ እውነት አዘንባይ ሲኾን የአብርሃምን መንገድ መራኝ፡፡ እርሱም ከአጋሪዎቹ አልነበረም» በል፡፡«ስግደቴ፣ እርዴም፣ ሕይወቴም፣ ሞቴም ለዓለማት ጌታ ለአላህ ነው» በል፡፡«ለእርሱ ተጋሪ የለውም፡፡ በዚህም (በማጥራት) ታዘዝኩ፡፡ እኔም የሙስሊሞች መጀመሪያ ነኝ» (በል)፡፡" *አል-አንዓም፡ 161-163*

በሐዲስ ዉስጥም እንዲህ ይላል "ከአላህ ሌላ ላለው ነገር ያረደን ሰው አላህ ረግመውታል" ይላል፡፡ ስለትም ለአላህ ብቻ ሲለመሆኑ ማስረጃው የአላህ (ሱ.ወ) ቃል ነው፡-

"(ዛሬ) በስለታቸው ይሞላሉ፡፡ መከራው ተሰራጪ የኾነንም ቀን ይፈራሉ፡፡" *አል-ኢንሳን፡7*

## ሁለተኛው መሰረታዊ መርህ

ሁለተኛ መርህ እስልምና ኀይማኖትን በማስረጃው ማወቅ ነው:: እሱም በተውሒድ ለአላህ መታዘዝ፣ ትእዛዙን በመተግበር እጅ እግርን ለሱ መስጠትና ከሽርክ መጥራት ነው:: እሱ ሦስት ደረጃ አለው:: እነሱም:- እስላም፣ ኢማንና ኢሕሳን ናቸው:: ሦስቱም ደረጃዎች የራሳቸው ማእዘናት አላቸው::

## የመጀመሪያ ደረጃ

የእስላም ማእዘናት 5 (አምስት) ናቸው:: እነሱም:- ከአላህ ሌላ በሐቅ የሚመለክ እንደ ሌለ መመስከርና ሙሐመድ የአላህ መልእክተኛ መሆናቸውን መመስከር፣ ስርዓቱን ጠብቀው ሳላትን መስገድ፣ ዘካን መስጠት፣ የረመዳን ወር መፆምና ሐጅ ማድረግ ናቸው:: የሸሃደተይን (ሁለቱ ምስካሬዎች) ማስረጃው የአላህ (ሱ.ወ) ቃል ነው:-

﴿ شَهِدَ ٱللَّهُ أَنَّهُۥ لَآ إِلَٰهَ إِلَّا هُوَ وَٱلۡمَلَٰٓئِكَةُ وَأُوْلُواْ ٱلۡعِلۡمِ قَآئِمَۢا بِٱلۡقِسۡطِۚ لَآ إِلَٰهَ إِلَّا هُوَ ٱلۡعَزِيزُ ٱلۡحَكِيمُ ﴾ [آل عمران، ١٨]

“አላህ በማስተካከል የቆመ (አስተናባሪ) ሲኾን ከእርሱ በስተቀር ሌላ አምላክ የሌለ መኾኑን መሰከረ:: መላእክቶችና የዕውቀት ባለቤቶችም (እንደዚሁ መሰከሩ):: ከእርሱ በስተቀር ሌላ አምላክ የለም:: አሸናፊው ጥበበኛው ነው::” *አሊ-ዒምራን:18*

ትርጉሟም:- ከአላህ ሌላ በሐቅ የሚመለክ አምላክ የለም ማለት ሲሆን “ላ እላሀ” የሚለው ቃል ከአላህ ሌላ የሚመለከውን ሁሉ ማስወገድ ነው፤ “ኢለሏህ” የሚለው ደግሞ አምልኮትን ለአላህ ብቻ

ማረጋገጥ ነው፡፡ እሱ በንግስናው ዉስጥ አጋር እንደ ሌለው ሁሉ በአምልኮቱ ዉስጥም አጋር የለዉም፡፡ የዚህን ትርጉም የሚያብራራ ቀጣዩ የአላህ (ሱወ) ቃል ነው፡-

﴿ وَإِذْ قَالَ إِبْرَٰهِيمُ لِأَبِيهِ وَقَوْمِهِۦٓ إِنَّنِى بَرَآءٌ مِّمَّا تَعْبُدُونَ ﴿٢٦﴾ إِلَّا ٱلَّذِى فَطَرَنِى فَإِنَّهُۥ سَيَهْدِينِ ﴿٢٧﴾ وَجَعَلَهَا كَلِمَةًۢ بَاقِيَةً فِى عَقِبِهِۦ لَعَلَّهُمْ يَرْجِعُونَ ﴾ [الزخرف: ٢٦-٢٨]

"ኢብራሂምም ለአባቱና ለሕዝቦቹ ባለ ጊዜ (አስታውስ)፡፡ «እኔ ከምትግገዙት ሁሉ ንጹሕ ነኝ፡፡ከዚያ ከፈጠረኝ በስተቀር (አልገዛም)፡፡ እርሱ በእርግጥ ይመራኛልና፡፡» (ይህች ቃል) በዝርዮቹም ውስጥ ወደሷ ይመለሱ ዘንድ (ባንድ አምላክ ማመንን) ቀሪ ቃል አደረጋት፡፡"

*አዝ-ዙኽሩፍ፡26-28*

﴿قُلْ يَٰٓأَهْلَ ٱلْكِتَٰبِ تَعَالَوْا۟ إِلَىٰ كَلِمَةٍ سَوَآءٍۭ بَيْنَنَا وَبَيْنَكُمْ أَلَّا نَعْبُدَ إِلَّا ٱللَّهَ وَلَا نُشْرِكَ بِهِۦ شَيْـًٔا وَلَا يَتَّخِذَ بَعْضُنَا بَعْضًا أَرْبَابًا مِّن دُونِ ٱللَّهِ ۚ فَإِن تَوَلَّوْا۟ فَقُولُوا۟ ٱشْهَدُوا۟ بِأَنَّا مُسْلِمُونَ ﴾ [آل عمران: ٦٤]

"የመጽሐፉ ባለቤቶች ሆይ! በእኛና በእናንተ መካከል ትክክል ወደ ኾነች ቃል ኑ፡፡ (እርሷም) አላህን እንጅ ሌላን ላንገዛ፣ በርሱም ምንንም ላናጋራ፣ ከፊላችንም ከፊሉን ከአላህ ሌላ አማልክት አድርጎ ላይይዝ ነው" በላቸው፡፡ እምቢ ቢሉም፡- እኛ ሙስሊሞች መኾናችንን መስክሩ በሏቸው፡፡" *ኣሊ-ዒምራን፡ 64*

ሙሐመድ የአላህ መልእክተኛ ናቸው ለሚለው ምስካሬ ማስረጃው የአላህ (ሱ.ወ) ቃል ነው፡-

﴿لَقَدْ جَآءَكُمْ رَسُولٌ مِّنْ أَنفُسِكُمْ عَزِيزٌ عَلَيْهِ مَا عَنِتُّمْ حَرِيصٌ عَلَيْكُم بِٱلْمُؤْمِنِينَ رَءُوفٌ رَّحِيمٌ ﴾ [التوبة: ١٢٨]

“ከጎሳችሁ የሆነ ችግራችሁ በእርሱ ላይ ጽኑ የሆነ፣ በእናንተ (እምነት) ላይ የሚጓጓ፣ በምእምናን (ላይ) ርኅሩኅ አዛኝ የኾነ መልክተኛ በእርግጥ መጣላችሁ፡፡” *አት-ተውባ፡128*

ሙሐመድ የአላህ መልእክተኛ ናቸው የሚል ምስካሬ ትርጉም ቀጣዩን ነጥቦችን ያስጨብጣል፡-

01 ያዘዙትን መታዘዝ፣

02 እሳቸው የተናገሩትን እውነት ብሎ መቀበል፣

03 እርሳቸው የከለከሉትንና የተቆጡትን መከልከል አና

04 አላህ ራሱ በደነገገው ወይም መልእከተኛው በደነገጉት ብቻ አላህን መገዛት ናቸው፡፡

የሰላት፣ የዘካና የተውሒድ ተፍሲር ማስረጃቸው የአላህ (ሱ.ወ) ቃል ነው፡-

﴿وَمَآ أُمِرُوٓاْ إِلَّا لِيَعۡبُدُواْ ٱللَّهَ مُخۡلِصِينَ لَهُ ٱلدِّينَ حُنَفَآءَ وَيُقِيمُواْ ٱلصَّلَوٰةَ وَيُؤۡتُواْ ٱلزَّكَوٰةَۚ وَذَٰلِكَ دِينُ ٱلۡقَيِّمَةِ﴾ [البينة: ٥]

“አላህን ሃይማኖትን ለእርሱ ብቻ አጥሪዎች፣ ቀጥተኞች ኾነው ሊግገዙት፣ ሰላትንም አስተካክለው ሊሰግዱ፣ ዘካንም ሊሰጡ እንጅ ያልታዘዙ ሲኾኑ (ተለያዩ)፡፡ ይህም የቀጥተኛይቱ (ሃይማኖት) ድንጋጌ ነው፡፡” *አል-በይና፡5*

የፆም ማስረጃ ቀጣዩ የአላህ (ሱ.ወ) ቃል ነው፡-

﴿يَٰٓأَيُّهَا ٱلَّذِينَ ءَامَنُواْ كُتِبَ عَلَيۡكُمُ ٱلصِّيَامُ كَمَا كُتِبَ عَلَى ٱلَّذِينَ مِن قَبۡلِكُمۡ لَعَلَّكُمۡ تَتَّقُونَ﴾ [البقرة: ١٨٣]

“እናንተ ያመናችሁ ሆይ! ጾም በነዚያ ከናንተ በፊት በነበሩት (ሕዝቦች) ላይ እንደ ተጻፈ በናንተም ላይ ተጻፈ (ተደነባ) ልትጠነቀቁ ይከጀላልና፡፡” *አልበቀራ፡183*

የሐጅ ማስረጃ ቀጣዩ የአላህ (ሱ.ወ) ቃል ነው፡-

﴿وَلِلَّهِ عَلَى ٱلنَّاسِ حِجُّ ٱلْبَيْتِ مَنِ ٱسْتَطَاعَ إِلَيْهِ سَبِيلًا ۚ وَمَن كَفَرَ فَإِنَّ ٱللَّهَ غَنِىٌّ عَنِ ٱلْعَٰلَمِينَ﴾ [آل عمران: ٩٧]

“ለአላህም በሰዎች ላይ ወደርሱ መኼድን በቻለ ሁሉ ላይ ቤቱን መጎብኘት ግዴታ አለባቸው፡፡ የካደም ሰው አላህ ከዓለማት ሁሉ የተብቃቃ ነው፡፡” *አሊ ዒምራን፡97*

## ሁለተኛው የኢስላም ደረጃ

ሁለተኛው የኢስላም እርከን ኢማን ሲሆን እሱ ሰባ ምናምን ቅርንጫፍ አለው፡፡ ከዚህ ሁሉ አንጋፋው “ላ እላሀ ኢለላህ” ሲሆን አነስተኛው ደግሞ ሰዎችን የሚያስቸግሩ ነገሮችን ማስወገድ ነው፡፡ እፍረትም (ሐያእም) የኢማን ቅርንቻፍ ነው፡፡ የኢማን ማእዘናት ስድስት ናቸው፡፡ እነሱም፡- በአላህ ማመን፣ በመላእክቶቹ፣ በመጽሐፍቶቹ፣ በመልእክተኞቹ፣ በአኺራ (መጨረሻው ቀን) እና ደግሞ ሆነ ክፉ በአላህ ቀደር (ዉሳኔ) ማመን ነው፡፡ የነዚህ ስድስቱ ማእዘናት ማስረጃቸው ቀጣዩ የአላህ (ሱ.ወ) ቃል ነው፡-

﴿لَّيْسَ ٱلْبِرَّ أَن تُوَلُّوا۟ وُجُوهَكُمْ قِبَلَ ٱلْمَشْرِقِ وَٱلْمَغْرِبِ وَلَٰكِنَّ ٱلْبِرَّ مَنْ ءَامَنَ بِٱللَّهِ وَٱلْيَوْمِ ٱلْءَاخِرِ وَٱلْمَلَٰٓئِكَةِ وَٱلْكِتَٰبِ وَٱلنَّبِيِّۦنَ﴾ [البقرة: ١٧٧]

“መልካም ሥራ ፊቶቻችሁን ወደ ምሥራቅና ምዕራብ አቅጣጫ ማዞር

አይደለም፡፡ ግን መልካም ሥራ በአላህና በመጨረሻው ቀን፣ በመላእክትም፣ በመጻሕፍትም፣ በነቢያትም፣ ያመነ ሰው (ስራ) ነው፡፡" *አልበቀራ፡177*

በቀደር (በአላህ ውሳኔ) ማመን ማስረጃው የአላህ (ሱ.ወ) ቃል ነው፡

﴿إِنَّا كُلَّ شَيۡءٍ خَلَقۡنَٰهُ بِقَدَرٖ﴾ [القمر: ٤٩]

"እኛ ሁሉን ነገር በቀደር ፈጠርነው፡፡" *አልቀመር፡49*

## ሦስተኛው የኢስላም ደረጃ

ሦስተኛው የኢስላም እርከን ኢሕሳን (ዒባዳን አሳምሮ መስራት) ነው፡፡ "እህሳን" አንድ ማእዘን ብቻ ሲሆን እሱም "እሕሳን" ማለት አላህን ልክ እንደምታየው ሆነህ መገዛትህ ነው፤ አንተ ባታየዉም እሱ ያየሃልና፡፡" ማስረጃውም የአላህ (ሱ.ወ) ቃል ነው፡-

﴿إِنَّ ٱللَّهَ مَعَ ٱلَّذِينَ ٱتَّقَواْ وَّٱلَّذِينَ هُم مُّحۡسِنُونَ﴾ [النحل: ١٢٨]

"አላህ ከእነዚያ ከሚፈሩትና ከእነዚያም እነሱ መልካም ሠሪዎች ከኾኑት ጋር ነውና፡፡" *አን-ነሕል፡128*

﴿وَتَوَكَّلۡ عَلَى ٱلۡعَزِيزِ ٱلرَّحِيمِ ٢١٧ ٱلَّذِي يَرَىٰكَ حِينَ تَقُومُ ٢١٨ وَتَقَلُّبَكَ فِي ٱلسَّٰجِدِينَ ٢١٩ إِنَّهُۥ هُوَ ٱلسَّمِيعُ ٱلۡعَلِيمُ﴾ [الشعراء: ٢١٧-٢٢٠]

"አሸናፊ አዛኝ በኾነው (ጌታህ) ላይም ተጠጋ፡፡በዚያ ለሶላት በምትቆም ጊዜ በሚያይህ፡፡በሰጋጆች ውስጥ መዘዋወርህንም (በሚያየው ጌታህ ላይ ተጠጋ)፡፡እነሆ እርሱ ሰሚው ዐዋቂው ነውና፡፡" *አሽ-ሹዐራእ፡217-220*

﴿وَمَا تَكُونُ فِي شَأۡنٖ وَمَا تَتۡلُواْ مِنۡهُ مِن قُرۡءَانٖ وَلَا تَعۡمَلُونَ مِنۡ عَمَلٍ إِلَّا كُنَّا عَلَيۡكُمۡ

شُهُودًا إِذْ تُفِيضُونَ فِيهِ ۚ وَمَا يَعْزُبُ عَن رَّبِّكَ مِن مِّثْقَالِ ذَرَّةٍ فِي الْأَرْضِ وَلَا فِي السَّمَاءِ وَلَا أَصْغَرَ مِن ذَٰلِكَ وَلَا أَكْبَرَ إِلَّا فِي كِتَابٍ مُّبِينٍ ﴾ [يونس: ٦١]

“(ሙሐመድ ሆይ!) በማንኛውም ነገር ላይ አትሆንም፣ ከርሱም ከቁርኣን አታነብም፣ ማንኛውንም ሥራ (አንተም ሰዎቹም) አትሠሩም በገባችሁበት ጊዜ በናንተ ላይ ተጠባባቂዎች ብንሆን እንጂ፡፡ በምድርም ሆነ በሰማይ የብናኝ ክብደት ያክል ከጌታህ (ዕውቀት) አይርቅም፡፡ ከዚያም ያነሰ የተለቀም የለም፤ በግልጹ መጽሐፍ ውስጥ የተጻፈ ቢሆን እንጂ፡፡” *ዩኑስ፡61*

ከሐዲስ ደግሞ ማስረጃው ታዋቂው የጅብሪል ሐዲስ ነው፡-

عن عمر بن الخطاب ﵁ قال: بينما نحن جلوس عند رسول الله ﷺ ذات يوم، إذ طلع علينا رجل شديد بياض الثياب، شديد سواد الشعر، لا يرى عليه أثر السفر، ولا يعرفه منا أحد، حتى جلس إلى النبي ﷺ فأسند ركبته إلى ركبتيه، ووضع كفيه على فخذيه، وقال: يا محمد أخبرني عن الإسلام، فقال له: «الإسلام أن تشهد أن لا إله إلا الله وأن محمدا رسول الله، وتقيم الصلاة وتؤتي الزكاة، وتصوم رمضان، وتحج البيت إن استطعت إليه سبيلا»، قال: صدقت، فعجبنا له يسأله ويصدقه، قال: أخبرني عن الإيمان، قال: «أن تؤمن بالله، وملائكته، وكتبه، ورسله، واليوم الآخر، وتؤمن بالقدر خيره وشره»، قال: صدقت، قال : فأخبرني عن الإحسان، قال: «أن تعبد الله كأنك تراه، فإن لم تكن تراه فإنه يراك»، قال: فأخبرني عن الساعة، قال: «ما المسؤول بأعلم من السائل»، قال: فأخبرني عن أماراتها، قال: «أن تلد الأمة ربتها، وأن ترى الحفاة العراة العالة رعاء الشاء يتطاولون في البنيان»، ثم انطلق فلبث مليا، ثم قال: «يا عمر، أتدري من السائل؟»، قلت: الله ورسوله أعلم، قال: «فإنه جبريل أتاكم يعلمكم دينكم». رواه مسلم

ከዑመር ቢን አልኸጣብ (ረ.ዐ) እንደተላለፈው እንዲህ አሉ፡- “ከእለታት አንድ ቀን ከነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) ጋር ተቀማምጠን እያለን አንድ በጣም ነጭ የሆነ ልብስ የለበሰ ጸጉሩ በጣም የጦቆረ የጉዞ ምልክት የማይታይበት ከኛም ዉስጥ ማንም የማያውቀዉ ሰዉ ብቅ አለ፡፡ ጉልበቶቹን ከነብዩ ጉልበቶች ጋር አሳክቶ መዳፎቹን ደግሞ ታፋዎቹ ላይ አድርጎ ተቀመጠ፡፡ ከዚያም “ሙሐመድ ሆይ! ሰለ ኢስላም ንገሩኝ” አላቸዉ፤፤ የአላህ መልዕክተኛም «ኢስላም ከአላህ ሌላ በሐቅ የሚመለክ አምላክ እንደሌለና ሙህመድ የአላህ መልዕክተኛ መሆናቸውን መመስከር፣ ሰላትን ደንቡን ጠብቆ መስገድ፤ ዘካ መስጠት፤ የረመዳን ወር መጾም፤አቅሙ ለፈቀዴለት ሰዉ ሀጅ ማድረግ ነዉ» በማለት መለሱለት፡፡ ሰዉየዉም “እውነት ተናገርክ” አላቸው፡፡ ዑመርም እንዲህ አለ “በሱ ተገረምን! እሳቸዉን ይጠይቃል፤ መልሶ እውነት ተናገርክ ይላል፡፡” ሰዉየው ቀጠለና “ስለ ኢማን ንገረኝ” አላቸው፡፡ የአላህ መልእካተኛ (ሰ.ዐ.ወ) እንዲህ አሉ፡- “ኢማን ማለት በአላህ ማመን፣ በመላእክቶቹ፣ በመጽሐፍቶቹ፣ በመልእክተኞቹ፣ በአኺራ (መጨረሻው ቀን) እና በጀም ከፋም በአላህ ቀደር (ዉሳኔ) ማመን ነው፡፡” ሰዉየዉም እውነት ተናገርክ አላቸው፡፡ ከዛም ሰዉየው ቀጠለና ስለ ኢሕሳን ንገረኝ አላቸው፡፡ የአላህ መልእካተኛ (ሰ.ዐ.ወ) እንዲህ አሉ፡- “እሕሳን” ማለት አላህን እንደሚትመለከት ሆነህ መገዛትህ ነው፤ አንተ ባታየዉም እሱ ያየሃልና፡፡” ሰዉየውም “የቅያማ ሰዓቷን ንገረኝ” አላቸው፡፡ የአላህ መልእካተኛ (ሰ.ዐ.ወ) እንዲህ አሉ፡- “ተጠያቂው ከጠያቂው የበለጠ የሚያውቅ አይደለም፡፡” ሰዉየው ቀጠለና “ምልክቶቿን ንገረኝ” አላቸው፡፡ የአላህ መልእካተኛም (ሰ.ዐ.ወ) አሉት፡- “ባርያ ጌታዋን

መውለድ፣ ጫማ የሌላቸው የታረዙ ደሃዎች የፍየል ጠባቂዎች የነበሩት ህንጻ ለመስራት ሲሽቀዳደሙ ማየትህ ነው፡፡” ሰዉየው ተነስቶ ሄዴ፤ ብዙ ቆየንና የአላህ መልእካተኛ (ሰ.ዐ.ወ) “እንተ ዑመር ሆይ! ጠያቂው ማን እንደ ሆነ ታቃላችሁን?” አሉ፡፡ “አላህና መልእክተናው ያውቃሉ” አልን፡፡ የአላህ መልእካተኛም (ሰ.ዐ.ወ) “እርሱ ጅብሪል ነው፤ የኀይማኖታችሁን ጉዳይ ሊያስተምራቹህ መጣቹህ” አሉ፡፡ *ሙስሊም ዘግበውታል*

## ሦስተኛ መሰረታዊ መርህ

ነቢያቹህ ሙሐመድን (ሰ.ዐ.ወ) ማወቅ

እርሳቸው ሙሐመድ ቢን ዐብደላህ ቢን ዐብዱልሙጠልብ ቢን ሃሺም ናቸው፡፡ ሃሺም ከቁረይሽ ጎሳ ነው፤ ቁረይሽም ከዐረቦች ናቸው፡፡ ዐረቦች ደግሞ የኢስማኢል ቢን ኢብራሂም (አላህ ወዳጅ) ዙርዮች ናቸው፡፡ አላህ በሱና በነቢያችን ላይ ምርጥ እዝነትና ሰላም ያስፍን፡፡

የነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) እድሜ ስልሳ ሶስት አመት ነበር፡፡ ከዚህ ዉስጥ አርባ አመት ከነቢይነት በፊት ነበር፡፡ ሃያ ሦስት አመት ደግሞ ነቢይና መልእክተኛ ሆነው አሳለፉ፡፡ በ“እቀረእ” ነቢይ ተደረጉ፤ በ“አልሙደስር” ደግሞ መልእክተኛ ሆኑ፡፡ አገራቸው መካ ነበር፡፡ ከሽርክ በማስጠንቅና ወደ ተውሒድ በመጣራት አላህ ላካቸው፡፡ ማስረጃውም የአላህ (ሱ.ወ) ቃል ነው፡-

﴿يَٰٓأَيُّهَا ٱلۡمُدَّثِّرُ ① قُمۡ فَأَنذِرۡ ② وَرَبَّكَ فَكَبِّرۡ ③ وَثِيَابَكَ فَطَهِّرۡ ④ وَٱلرُّجۡزَ فَٱهۡجُرۡ ⑤ وَلَا تَمۡنُن تَسۡتَكۡثِرُ ⑥ وَلِرَبِّكَ فَٱصۡبِرۡ﴾ [المدثر: ١-٧]

“አንተ (ልብስህን) ደራቢው ሆይ! ተነስ አስጠንቅቅም፡፡ ጌታህንም አክብር፡፡ ልብስህንም አጥራ፡፡ ጣዖትንም ራቅ፡፡ ማብዛትንም የምትፈልግ ኾነህ አትለግስ፡፡ ለጌታህም (ትዕዛዝ) ታገሥ፡፡” *አልሙደሲር፡ 1-7*

*“ተነስ አስጠንቅቅ”* የተባለው ከሽርክ ማስጠንቅና ወደ ተውሒድ መጣራት ነው፡፡ *“ጌታህንም አክብር”* የተባለው በተውሂድ እሱን ማላቅ ነው፡፡ *“ልብስህንም አጥራ”* ማለት ስራህን ከሽርክ አጥራ ማለት ሲሆን “ሩጅዝ” የተባለዉም ጣዖት ነው፡፡ ከሷ መራቅ ማለት እሷንና እሷን የሚያመልኩ ሰዎችን መተዉና ከነሱ መንፃት ነው፡፡ አስር አመት በዚህ ላይ ቆይተው ወደ ተውሒድ ሲጣሩ ነበሩ፡፡ ከ 10 አመት በኋላ ወደ ሰማይ ዐረጉና አምስቱ ሰላት ግዴታ ተደረገባቸው፡፡ መካ ዉስጥ ሶስት አመት ሰገዱ፤ ከዚያ በኋላ ወደ መዲና መሰሰደድ ታዘዙ፡፡ ስደት ማለት ከሽርክ አገር ወደ እስላም አገር መሸሽ ነው፡፡ ከሽርክ አገር ወደ እስላም አገር መሰደድ በዚህ ኡማ ላይ ግዴታ ነው፡፡ ማስረጃውም የአላህ (ሱ.ወ) ቃል ነው፡-

﴿ إِنَّ ٱلَّذِينَ تَوَفَّىٰهُمُ ٱلْمَلَـٰٓئِكَةُ ظَالِمِىٓ أَنفُسِهِمْ قَالُوا۟ فِيمَ كُنتُمْ ۖ قَالُوا۟ كُنَّا مُسْتَضْعَفِينَ فِى ٱلْأَرْضِ ۚ قَالُوٓا۟ أَلَمْ تَكُنْ أَرْضُ ٱللَّهِ وَٰسِعَةً فَتُهَاجِرُوا۟ فِيهَا ۚ فَأُو۟لَـٰٓئِكَ مَأْوَىٰهُمْ جَهَنَّمُ ۖ وَسَآءَتْ مَصِيرًا ﴿٩٧﴾ إِلَّا ٱلْمُسْتَضْعَفِينَ مِنَ ٱلرِّجَالِ وَٱلنِّسَآءِ وَٱلْوِلْدَٰنِ لَا يَسْتَطِيعُونَ حِيلَةً وَلَا يَهْتَدُونَ سَبِيلًا ﴿٩٨﴾ فَأُو۟لَـٰٓئِكَ عَسَى ٱللَّهُ أَن يَعْفُوَ عَنْهُمْ ۚ وَكَانَ ٱللَّهُ عَفُوًّا غَفُورًا ﴾ [النساء: ٩٧-٩٩]

“እነዚያ (ለእምነት ባለመሰደድ) ነፍሶቻቸውን በዳዮች ኾነው መላእክት የገደሉዋቸው (መላእክት ለነርሱ) «በምን ነገር ላይ ነበራችሁ?» አሏቸው፡፡ «በምድር ውስጥ ደካሞች ነበርን» አሉ፡፡ «የአላህ ምድር

ትሰደዱባት ዘንድ ሰፊ አልነበረችምን?» አሉዋቸው፡፡ እነዚያም መኖሪያቸው ገሀነም ናት፡፡ በመመለሻነትም ከፋች! ግን ከወንዶችና ከሴቶች ከሕፃኖችም ሲኾኑ (ለመውጣት) መላን የማይችሉና መንገድንም የማይመሩ ደካሞች (ቅጣት የለባቸውም) እነዚያም አላህ ከእነርሱ ይቅርታ ሊያደርግ ይሻል፡፡ አላህም ይቅር ባይ መሓሪ ነው፡፡" *አን-ኒሳእ፡97-99*

﴿ يَـٰعِبَادِىَ ٱلَّذِينَ ءَامَنُوٓا۟ إِنَّ أَرْضِى وَٰسِعَةٌ فَإِيَّـٰىَ فَٱعْبُدُونِ ﴾ [العنكبوت: ٥٦]

"እናንተ ያመናችሁ ባሮቼ ሆይ! ምድሬ በእርግጥ ሰፊ ናት፤ (ብትቸገሩ ተሰደዱና እኔን ብቻ ተገዙኝ፡፡" *አል-ዐንከቡት፡56*

ኢማም አልበገዊ አላህ ይዘንለትና እንዲህ አለ፡- "የዚህ አንቀፅ መውረድ ምክንያት መካ ዉስጥ የነበሩ ያልተሰደዱ ሙስሊሞች ናቸው፤ አላህ በእምነት ስም ጠራቸው፡፡" የስደት ማስረጃ ከሐዲስ ደግሞ ቀጣይ የነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) ቃል ነው፡- "ተውበት እስከቋረጥ ድረስ ስደት አይቋረጥም፤ ተውበት ደግሞ ፀሐይ ከመግቢያዋ እስክትወጣ ድረስ አይቋረጥም፡፡" በመዲና ዉስጥ ከተረጋጉ በኋላ በሌሎች የእስላም ድንጋጌ፣ በዘካ፣ ፆም፣ ሐጅ፣ አዛን፣ ጅሃድ፣ በመልካም ማዘዝ፣ ከመጥፎ መከልከል እና በሌሎችም የእስላም ድንጋጌ ታዘዙ፡፡ በዚህ ላይ 10 ዓመት ቆዩ፡፡ ከዚያ በኋላ ነቢዩ (ሰ.ዐ.ቀ) ሞቱ፡፡ ኀይማኖታቸው ግን ቀርተዋል፡፡ ይህ ራሱ ኀይማኖታቸው ነው፡፡ ኡማዉን ሳያመላክቱ ያለፉት መልካም ነገር የለም፤ እንደዚያዉም ያላስጠነቀቁት መጥፎ ነገር የለም፡፡ ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) ኡማዉን ያመላከቱ መልካም ነገር ተውሒድና ሌሎች አላህ የሚወዳቸው

ነገራቶች ናቸው፡፡ የስጠነቀቁት ክፉ ነገር ደግሞ ሽርክና ማንኛዉም አላህ የሚጠላቸው ነገራቶች ናቸው፡፡ አላህ ወደ መላው የሰው ልጅ ላካቸው፡፡ እርሳቸዉን መታዘዝ በጋኔኖችና በሰው ልጆች ላይ ግዴታ አድርጓል፡፡ ማስረጃውም የአላህ (ሱ.ወ) ቃል ነው፡

﴿قُلۡ يَٰٓأَيُّهَا ٱلنَّاسُ إِنِّي رَسُولُ ٱللَّهِ إِلَيۡكُمۡ جَمِيعًا ٱلَّذِي لَهُۥ مُلۡكُ ٱلسَّمَٰوَٰتِ وَٱلۡأَرۡضِ﴾ [الأعراف: ١٥٨]

“እናንተ ሰዎች ሆይ! እኔ ወደናንተ ወደሁላችሁም የአላህ መልክተኛ ነኝ” በላቸው፡፡ *አል-አዕራፍ፡158*

አላህ በእርሳቸው ዲኑን ሞልቶታል፡፡ ማስረጃውም የአላህ (ሱ.ወ) ቃል ነው፡-

﴿ٱلۡيَوۡمَ أَكۡمَلۡتُ لَكُمۡ دِينَكُمۡ وَأَتۡمَمۡتُ عَلَيۡكُمۡ نِعۡمَتِي وَرَضِيتُ لَكُمُ ٱلۡإِسۡلَٰمَ دِينٗا﴾ [المائدة: ٣]

“ዛሬ ሃይማኖታችሁን ለናንተ ሞላሁላችሁ፡፡ ጸጋዬንም በናንተ ላይ ፈጸምኩ፡፡ ለእናንተም ኢስላምን ከሃይማኖት በኩል ወደድኩ፡፡” *አልማኢዳ፡ 3*

ለመሞታቸዉም ማስረጃው የአላህ (ሱ.ወ) ቃል ነው፡-

﴿إِنَّكَ مَيِّتٞ وَإِنَّهُم مَّيِّتُونَ ﴿٣٠﴾ ثُمَّ إِنَّكُمۡ يَوۡمَ ٱلۡقِيَٰمَةِ عِندَ رَبِّكُمۡ تَخۡتَصِمُونَ﴾

[الزمر: ٣٠– ٣١]

“አንተ ሟች ነህ፤ እነርሱም ሟቾች ናቸው፡፡ ከዚያም እናንተ በትንሣኤ ቀን እጌታችሁ ዘንድ ትከራከራላችሁ፡፡” *አዝ-ዙመር፡30-31*

ሰዎች ከሞት በኋላ ይቀሰቀሳሉ፡፡ ማስረጃው የአላህ (ሱ.ወ) ቃል ነው፡-

﴿مِنۡهَا خَلَقۡنَٰكُمۡ وَفِيهَا نُعِيدُكُمۡ وَمِنۡهَا نُخۡرِجُكُمۡ تَارَةً أُخۡرَىٰ﴾ [طه: ٥٥]

“ከእርሷ (ከምድር) ፈጠርናችሁ፡፡ በእርሷም ውስጥ እንመልሳችኋለን፡፡ ከእርሷም በሌላ ጊዜ እናወጣችኋለን፡፡” *ጣሃ፡55*

﴿وَٱللَّهُ أَنۢبَتَكُم مِّنَ ٱلۡأَرۡضِ نَبَاتٗا ١٧ ثُمَّ يُعِيدُكُمۡ فِيهَا وَيُخۡرِجُكُمۡ إِخۡرَاجٗا﴾ [نوح: ١٧-١٨]

“አላህም ከምድር ማብቀልን አበቀላችሁ፡፡ ከዚያም በውስጧ ይመልሳችኋል፡፡ ማውጣትንም ያወጣችኋል፡፡” *ኑሕ፡17-18*

ከተቀሰቀሱ በኋላ ዱንያ ላይ በሰሩት ነገር ተመርምሮ ይመነዳሉ፡፡ ማስረጃው የአላህ (ሱ.ወ) ቃል ነው፡-

﴿وَلِلَّهِ مَا فِي ٱلسَّمَٰوَٰتِ وَمَا فِي ٱلۡأَرۡضِ لِيَجۡزِيَ ٱلَّذِينَ أَسَٰٓـُٔواْ بِمَا عَمِلُواْ وَيَجۡزِيَ ٱلَّذِينَ أَحۡسَنُواْ بِٱلۡحُسۡنَى﴾ [النجم: ٣١]

“በሰማያት ያለውና በምድር ያለው ሁሉ የአላህ ነው፡፡ እነዚያን ያጠፉትን በሠሩት ሊቀጣ እነዚያን ያሳመሩትንም በመልካሚቱ (ገነት) ሊመነዳ (የጠመመውንና የቀናውን ያውቃል)፡፡” *አን-ነጅም፡31*

መቀስቀስን ያስተባበለ ሰው ከእስላም ይወጣል፡፡ ማስረጃው የአላህ (ሱ.ወ) ቃል ነው፡-

﴿زَعَمَ ٱلَّذِينَ كَفَرُوٓاْ أَن لَّن يُبۡعَثُواْۚ قُلۡ بَلَىٰ وَرَبِّي لَتُبۡعَثُنَّ ثُمَّ لَتُنَبَّؤُنَّ بِمَا عَمِلۡتُمۡۚ وَذَٰلِكَ عَلَى ٱللَّهِ يَسِيرٞ﴾ [التغابن: ٧]

“እነዚያ የካዱት በፍጹም የማይቀሰሱ መኾናቸውን አሰቡ፡ «አይደለም በጌታዬ እምላለሁ፡፡ በእርግጥ ትቀሰቀሳላችሁ፡፡ ከዚያም በሠራችሁት ሁሉ ትነገራላችሁ፡፡ ይህም በአላህ ላይ ቀላል ነው» በላቸው፡፡” *አት-ተጋቡን፡7*

አላህ (ሱ.ወ) ሁሉንም መልእክተኛ አብሳሪና አስጠንቃቂ አድርጓቸው ላከ፡፡ ማስረጃውም የአላህ (ሱ.ወ) ቃል ነው፡

﴿ رُّسُلًا مُّبَشِّرِينَ وَمُنذِرِينَ لِئَلَّا يَكُونَ لِلنَّاسِ عَلَى ٱللَّهِ حُجَّةُۢ بَعۡدَ ٱلرُّسُلِ ﴾ [النساء: ١٦٥]

“ከመልክተኞቹ በኋላ ለሰዎች በአላህ ላይ አስረጅ እንዳይኖር አብሳሪዎችና አስፈራሪዎች የኾኑን መልክተኞች (ላክን)፡፡ አላህም አሸናፊ ጥበበኛ ነው፡፡” *አን-ኒሳእ፡165*

የመልእክተኞች ሁሉ መጀመርያ ኑሕ ሲሆኑ መጨረሻቸው ደግሞ ሙሐመድ (ሰ.ዐ.ወ) ናቸው፡፡ እርሳቸው የነቢያቶች መደምደምያ ናቸው፡፡ ኑሕ የመልእክተኞች ሁሉ መጀመርያ ለመሆኑ ማስረጃው ቀጣይ የአላህ (ሱ.ወ) ቃል ነው፡-

﴿إِنَّآ أَوۡحَيۡنَآ إِلَيۡكَ كَمَآ أَوۡحَيۡنَآ إِلَىٰ نُوحٖ وَٱلنَّبِيِّـۧنَ مِنۢ بَعۡدِهِۦ﴾ [النساء: ١٦٣]

“እኛ ወደ ኑሕና ከርሱ በኋላ ወደ ነበሩት ነቢያት እንዳወረድን ወደ አንተም አወረድን፡፡” *አን-ኒሳእ፡163*

አላህ ወደ ሁሉም ሕዝቦች “አላህን በብቸኝነት መገዛት የሚያዛቸውና ጣዖትን ከማምለክ የሚከለክላቸውን” መልእክተኛ ከኑሕ እስከ ሙሐመድ (ሰ.ዐ.ወ) ድረስ ያሉትን ላከ፡፡ ማስረጃውም የአላህ (ሱ.ወ) ቃል ነው፡-

﴿ وَلَقَدۡ بَعَثۡنَا فِي كُلِّ أُمَّةٖ رَّسُولًا أَنِ ٱعۡبُدُواْ ٱللَّهَ وَٱجۡتَنِبُواْ ٱلطَّٰغُوتَ ﴾ [النحل: ٣٦]

“በየሕዝቡም ሁሉ ውስጥ «አላህን ተገዙ፤ ጣዖትንም ራቁ» በማለት መልክተኛን በእርግጥ ልከናል፡፡” *አን-ነሕል፡36*

አላህ በሁሉም ባሮቹ ላይ ጣዖትን መካድና በአላህ ማመን ግዴታ አድርጓል፡፡ ኢብን አልቀይም አላህ ይዘንላቸውና እንዲህ አሉ፡-

ጣኦት የሚባለው ሰዎች እርሱን በማምለክ፣ እርሱን በመከተል ወይም በመታዘዝ ድንበር ያለፉት ነው፡፡ ጣዖታት ብዙ ናቸው፡፡ ቀንደኞቹ ግን አምስት ናቸው፡፡ እነሱም፡-

ኢብሊስ (አላህ ይርገመው)፣

ወዶ የሚመለክ ሰው፣

ሰዎች እንዲያመልኩት ወደራሱ አምልኮት የሚጣራ ሰው፣

የሩቅ እውቀትን አውቃለው ያለ ሰዉና

አላህ ካወረደው ሌላ በሰው ሰራሽ ህግ የፈረደ ሰው ናቸው፡፡

ማስረጃውም ቀጣዩ የአላህ (ሱ.ወ) ቃል ነው፡-

﴿لَآ إِكۡرَاهَ فِي ٱلدِّينِۖ قَد تَّبَيَّنَ ٱلرُّشۡدُ مِنَ ٱلۡغَيِّۚ فَمَن يَكۡفُرۡ بِٱلطَّٰغُوتِ وَيُؤۡمِنۢ بِٱللَّهِ فَقَدِ ٱسۡتَمۡسَكَ بِٱلۡعُرۡوَةِ ٱلۡوُثۡقَىٰ لَا ٱنفِصَامَ لَهَاۗ وَٱللَّهُ سَمِيعٌ عَلِيمٌ﴾ [البقرة: ٢٥٦]

“በሃይማኖት ዉስጥ ማስገደድ የለም፡፡ ቅኑ መንገድ ከጠማማው በእርግጥ ተገለጠ፡፡ በጣዖትም የሚክድና በአላህ የሚያምን ሰው ለርሷ መበጠስ የሌላትን ጠንካራ ዘለበት በእርግጥ ጨበጠ፡፡ አላህም ሰሚ ዐዋቂ ነው፡፡” *አልበቀራ፡256*

ይህ የ“ላ እላሀ እለላህ” ትርጉም ነው፡፡ በነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) ሐዲስ ዉስጥ ቀጣዩ ይገኛል “የነገሮች ሁሉ ቁንጮ እስላም ነው፤ ምሰሶው ሰላት ሲሆን የላኛ ሻኛው በአላህ መንገድ ላይ መታገል ነው፡፡”

አላህ ሁሉንም አዋቂ ነው፡፡ የአላህ እዘነትና ሰላም በሙሐመድ፣ በቤተሰቦቻቸውና በባልደረቦቻቸው ላይ ይስፈን፡፡

# የሰላት መስፈርቶች፣ ማእዘናቱና ግዴታዎቹ

በአላህ ስም እጅግ በጣም ርኅሩህ በጣም አዛኝ በኾነው፡፡

## የሰላት መስፈርቶች ዘጠኝ ናቸው፡፡

እነሱም፡-

ሙስሊም መሆን፣ አእምሮው ጤናማ መሆን፣ መጥፎንና ጥሩን ነገር የሚለይ እድሜ ላይ መድረስ፣ ሐደስ[1]ን ማስወገድ፣ ነጃሳን ማስወገድ፣ ህፍረተ ገላን መሸፈን፣ የሰላት ወቅት መግባት፣ ወደ ቂብላ (ካዕባ) መዞር እና ኒያ ናቸው፡፡

## መስፈርት አንድ፡-

ሙስሊም መሆን፡፡ የዚህ ተቃራኒ ካፊር መሆን ሲሆን ካፊር ደግሞ የፈለገ ስራ ቢሰራም በርሱ ላይ ተመላሽ ይሆናል፡፡ ለዚህም ማስረጃው የአላህ (ሱ.ወ) ቃል ነው፡-

1 ሐደስ ማለት ዉዱእን ማጥፋት ወይም ጀናባ መሆን ማለት ነው፡፡ እርሱን ማስወገድ ማለት ዉዱእ ማድረግና መታጠብ ማለት ነው፡፡

﴿ مَا كَانَ لِلْمُشْرِكِينَ أَن يَعْمُرُوا مَسَاجِدَ اللَّهِ شَاهِدِينَ عَلَىٰ أَنفُسِهِم بِالْكُفْرِ ۚ أُولَٰئِكَ حَبِطَتْ أَعْمَالُهُمْ وَفِي النَّارِ هُمْ خَالِدُونَ ﴾ [التوبة: ١٧]

“ለከሓዲዎች በነፍሶቻቸው ላይ በክህደት የሚመሰክሩ ሲኾኑ የአላህን መስጊዶች ሊሠሩ አይገባቸውም፡፡ እነዚያ ሥራዎቻቸው ተበላሹ፡፡ እነሱም በእሳት ውስጥ ዘውታሪዎች ናቸው፡፡” *አት-ተውባ፡17*

﴿ وَقَدِمْنَا إِلَىٰ مَا عَمِلُوا مِنْ عَمَلٍ فَجَعَلْنَاهُ هَبَاءً مَّنثُورًا ﴾ [الفرقان: ٢٣]

“ከሥራም ወደ ሠሩት እናስባለን፡፡ የተበተነ ትቢያም እናደርገዋለን፡፡” *አልፉርቃን፡23*

## መስፈርት ሁለት፡

ጤናማ አእምሮ ያለው መሆን ነው፡፡ ተቃራኒው እብደት ነው፡፡ እብድ ደግሞ እስኪድን ድረስ ብእር ተነስቶለታል (ስራው አይፃፍበትም)፡፡ ማስረጃውም የነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) ቃል ነው፡- “ብእር ከሶስት ሰዎች ተነስቶላቸዋል፡ ያንቀላፋ ሰው እስከነቃ ድረስ፣ እብድ እስከድን ድረስ እና ህጻን ለአቅመ አዳም እስከደርስ ድረስ፡፡”

## መስፈርት ሶስት፡

ተምዩዝ (መጥፎንና ጥሩን ነገር የሚለይ እድሜ ላይ መድረስ) ነው፡፡ ተቃራኒውም ህጻንነት ሲሆን እሱም እስከ ሰባት አመት ይዘልቃል፡፡ ከዚያ በኋላ በሰላት ይታዘዛል፡፡ ማስረጃውም የነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) ቃል ነው፡- “ልጆቻችሁን ሰባት ዓመት ስሞላቸው ሰላትን እዘዙሃቸው፡፡ (ባይሰግዱ) አስር ዓመት ስሞላቸው በሷ ላይ ምቷቸው፡፡ በመኝታም ለያዩዋቸው፡፡”

## መስፈርት አራት፡

ሐደስን ማስወገድ፡፡ ይህም ማለት የሚታወቀው ዉዱእ ራሱ ነው፡፡ ይህ ሐደስ ዉዱን ያስገድዳል፡፡ የዉዱእ መስፈርቶች አስር ናቸው፡፡ እነሱም፡-

01 ሙስሊም መሆን፣

02 አእምሮው ጤናማ መሆን፣

03 መጥፎንና ጥሩ ነገርን የሚለይ እድሜ ላይ መድረስ፣

04 መነየት፣

05 ዉዱእ እስኪያጠናቅቁ ድረስ ላለማቋረጥ መወሰን፣

06 ዉዱእን የሚያፈርስን ነገር ማስወገድ፣

07 ከሱ በፊት በዉሃ ወይም በድንጋይ እስትንጃ ማድረግ፣

08 ዉሃው ንፁህና መጠቀሙ የተፈቀደ መሆን፣

09 ዉሃ ወደ ሰዉነት እንዳይደርስ የሚከለክልን ነገር ማስወገድ እና

10 ዉዱን የሚያጠፋ ነገር ከሰዉነቱ ለማይቋረጥ ሰው የሚሰግደው የሰላት ወቅት መግባት ናቸው፡፡

የዉዱእ ግዴታዎች ስድስት ናቸው፡፡ እነሱም፡-

01 ፊትን መታጠብ ሲሆን አፍን መጉመጥመጥና ዉሃን በአፍንጫ መሳብ ከዚው ይመደባል፡፡ ፊት የሚባለው ከላይ ወደታች ከጭንቅላት ፀጉር መብቀያ እስከ አገጭ ሲሆን በጎን ደግሞ ከጆሮ እስከ ጆሮ ይሆናል፡፡

02 ሁለቱን እጆች ከክርኖች ጋር ማጠብ

03 ሙሉ ራስን ከጆሮ ጭምር ማበስ

04 ሁለቱን እግሮች ከቁርጭምጭሚቶች ጋር ማጠብ

05 የተጠቀሱትን የዉዱን ድርጊቶች ቅደም ተከተል መጠበቅ እና

06 ድርጊቶቹን ማከታተል ናቸው፡፡

ማስረጃውም የአላህ (ሱ.ወ) ቃል ነው፡-

﴿يَـٰٓأَيُّهَا ٱلَّذِينَ ءَامَنُوٓا۟ إِذَا قُمْتُمْ إِلَى ٱلصَّلَوٰةِ فَٱغْسِلُوا۟ وُجُوهَكُمْ وَأَيْدِيَكُمْ إِلَى ٱلْمَرَافِقِ وَٱمْسَحُوا۟ بِرُءُوسِكُمْ وَأَرْجُلَكُمْ إِلَى ٱلْكَعْبَيْنِ﴾ [المائدة: ٦]

"እናንተ ያመናችሁ ሆይ! ወደ ሰላት በቆማችሁ (ለመቆም ባሰባችሁ) ጊዜ ፊቶቻችሁን፣ እጆቻችሁንም እስከ ክርኖች እጠቡ፡፡ ራሶቻችሁንም (በውሃ) አብሱ፡፡ እግሮቻችሁንም እስከ ቁርጭምጭሚቶች (እጠቡ)፡፡"
*አልማኢዳ፡6*

የቅደም ተከተል ማስረጃም የነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) ቃል ነው፡- "አላህ በጀመረው ነገር ጀምሩ፡፡" ዉዱን የማከታተል ማስረጃ ደግሞ በእግሩ ተረከዝ ላይ ሳንቲምን የሚያክል ዉሃ ሳይነካው የቀረውን ሰዉዬ ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) ዉዱእ እንዲደግም ማዘዛቸው ነው፡፡ ዋጅቡ ደግሞ ካስተወሱ "ብስምላህ" ማለት ነው፡፡ ዉዱእን የሚያበላሹ ነገሮች 8 (ስምንት) ናቸው፡፡ እነሱም፡-

01 ከሁለቱ የቆሻሻ ማውጫ መንገዶች የወጣ ሁሉ፣

02 ከሰዉነታችን ዉስጥ የሚወጣ ነጃሳ ነገር፣

03 በእንቅልፍና በመሳሰሉት ነገሮች አእምሮን መሳት፣

04 በግብረ ስጋ ስሜት ሴቶችን (ተቃራኒ ጾታን) መንካት፣

05 ሁለቱን ሀፍረተ ገላዎች ያለ ሽፋን መንካት፣

06 የግመል ስጋን መብላት፣

07 ጀናዛናን ማጠብ እና

08 ከእስሊምና መውጣት ናቸው፡፡ አላህ ከሱ ይጠብቀን

## መስፈርት አምስት፡

ነጃሳን ማስወገድ፡- ነጃሳን የሚናስወግደው ከሶስት ነገር ነው፡፡ እነሱም ከሰውነት፣ ከልብስና ከሰላት ቦታ ናቸው፡፡ ማስረጃውም የአላህ (ሱ.ወ) ቃል ነው፡-

﴿وَثِيَابَكَ فَطَهِّرْ﴾ [المدثر: ٤]

“ልብስህንም አጥራ፡፡” *አልሙደስር፡4*

## መስፈርት ስድስት፡

ሀፍረተገላን መሸፈን ነው፡፡ መልበስ እየቻለ ራቆቱን የሰገደ ሰው ሰላቱ ዉድቅ መሆኑን ዓሊሞች ተስማምተዋል፡፡ የወንድ ሀፍረተገላ ከእንብርት እስከ ጉልበት ሲሆን ሴት ባሮችም እንዲሁ ናቸው፡፡ ሌሎች ሴቶች ደግሞ ፊታቸው ሲቀር ሌላውን መሸፈን ግዴታ ነው፡፡ ማስረጃውም የአላህ (ሱ.ወ) ቃል ነው፡-

﴿يَٰبَنِيٓ ءَادَمَ خُذُواْ زِينَتَكُمْ عِندَ كُلِّ مَسْجِدٍ﴾ [الأعراف: ٣١]

“የአዳም ልጆች ሆይ! (ኀፍረተ ገላችሁን የሚሸፍኑትን) ጌጦቻችሁን በመስገጃው ሁሉ ዘንድ ያዙ፡፡” *አል-አዕራፍ፡31*

## መስፈርት ሰባት፡

የሰላቱ ወቅት መግባት ነው፡፡ ማስረጃውም የጅብሪል ሐዲስ ነው፡- ጅብሪል በመጀመሪያ ወቅትና በመጨረሻው ነቢዩን (ሰ.ዐ.ወ) አሰገደና ቀጥሎም እንዲህ አለ፡- “ሙሐመድ ሆይ! ሰላት በነዚህ ሁለቱ ወቅቶች መካከል ነው፡፡” ሌላ ማስረጃ የአላህ (ሱ.ወ) ቃል ነው፡-

﴿إِنَّ ٱلصَّلَوٰةَ كَانَتۡ عَلَى ٱلۡمُؤۡمِنِينَ كِتَٰبٗا مَّوۡقُوتٗا﴾ [النساء: ١٠٣]

“ሶላት በምእምናን ላይ በጊዜያት የተወሰነች ግዴታ ናትና፡፡” *አን-ኒሳእ፡103*

ሌላ የወቅት ማስረጃ የአላህ (ሱ.ወ) ቃል ነው፡-

﴿أَقِمِ ٱلصَّلَوٰةَ لِدُلُوكِ ٱلشَّمۡسِ إِلَىٰ غَسَقِ ٱلَّيۡلِ وَقُرۡءَانَ ٱلۡفَجۡرِۖ إِنَّ قُرۡءَانَ ٱلۡفَجۡرِ كَانَ مَشۡهُودٗا﴾ [الإسراء: ٧٨]

“ሶላትን ከፀሐይ መዘንበል እስከ ሌሊት ጨለማ ድረስ ስገድ፡፡ የጎህንም ሶላት ስገድ፡፡ የጎህ ሶላት (መላእክት) የሚጣዱት ነውና፡፡” *አል-ኢስራእ፡78*

## መስፈርት ስምንት፡

ወደ ቅብላ (ከዕባ) መዞር ነው፡፡ ማስረጃውም የአላህ (ሱ.ወ) ቃል ነው፡-

﴿قَدۡ نَرَىٰ تَقَلُّبَ وَجۡهِكَ فِي ٱلسَّمَآءِۖ فَلَنُوَلِّيَنَّكَ قِبۡلَةٗ تَرۡضَىٰهَاۚ فَوَلِّ وَجۡهَكَ شَطۡرَ ٱلۡمَسۡجِدِ ٱلۡحَرَامِۚ وَحَيۡثُ مَا كُنتُمۡ فَوَلُّواْ وُجُوهَكُمۡ شَطۡرَهُۥ﴾ [البقرة: ١٤٤]

“የፊትህን ወደ ሰማይ መገላበጥ በእርግጥ እናያለን፡፡ ወደምትወዳትም

ቂብላ እናዞርሃለን፡፡ ስለዚህ ፊትህን ወደ ተከበረው መስጊድ (ወደ ካዕባ) አግጣጫ አዙር፡፡ የትም ስፍራ ብትኾኑም (ስትሰግዱ) ፊቶቻችሁን ወደርሱ አግጣጫ አዙሩ፡፡" *አልበቀራ፡144*

## መስፈርት ዘጠኝ፡

መነየት ነው፡፡ ቦታው ልብ ሲሆን በአንደበት መናገር ቢድዓ ነው፡፡ ማስረጃውም የነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) ቃል ነው፡- "ስራዎች ትክክል ሆነው የሚገኙት ኒያ ሲኖር ብቻ ነው፡፡ ሁሉም ሰው የነየተውን ያገኛል፡፡"

# የሰላት ማእዘናት አስራ አራት ናቸው

የቻለ ሰው መቆም፣ወደ ሰላት መግቢያ ተክቢራ (አላሁ አክበር)፣ሱረት አልፋቲሓን ማንበብ፣ ሩኩዕ (ማጎንበስ)፣ ከሩኩዕ ቀጥ ብሎ መቆም፣ በሰባት አካላት ሱጁድ ማድረግ፣ ከሱጁዱ መነሳት፣ በሁለቱ ሱጁዶች መካከል መቀመጥ፣ በሁሉም የሰላት ስራዎች ዉስጥ መረጋጋት፣ በየማእዘናቱ መካከል ያለውን ቅደም ተከተል መጠበቅ፣ የመጨረሻውን አት-ተሕያቱን መቅራት፣ ለሱም መቀመጥ፣ በነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) ላይ ሰለዋት ማውረድ እና በሁለቱም ጎን ማሰላመት ናቸው።

## አንደኛው ማእዘን፡

የቻለ ሰው መቆም ነው። ማስረጃውም የአላህ (ሱ.ወ) ቃል ነው፡-

﴿حَـٰفِظُواْ عَلَى ٱلصَّلَوَٰتِ وَٱلصَّلَوٰةِ ٱلْوُسْطَىٰ وَقُومُواْ لِلَّهِ قَـٰنِتِينَ﴾ [البقرة: ٢٣٨]

"በሶላቶች (በተለይ) በመካከለኛይቱ ሶላት ላይ ተጠባበቁ። ታዛዦች ኾናችሁም ለአላህ ቁሙ።" *አልበቀራ፡238*

## ሁለተኛው ማእዘን፡

ወደ ሰላት መግቢያ ተክቢራ (አላሁ አክበር) ማለት ነው። ማስረጃውም የነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) ቃል ነው፡-"(ሰላት ውስጥ የማይፈቀዱ ነገሮችን)

እርም የሚታደርግ ተከቢራ ሲትሆን የተፈቀደ የሚታደርግ ደግሞ ማሰላመት ናት፡፡” ከሷ ቀጥሎ የመክፈቻ ዱዓእ ያደርጋል፡፡ እሱም፡-

«سبحانك اللهم وبحمدك وتبارك اسمك وتعالى جدك ولا إله غيرك»

“ሱብሓነከ-ልላሁመ፥ ወቢሐምዲከ፥ ወተባረከ ኢስሙከ፥ ወተዓላ ጀድዱከ፥ ወላ ኢላሀ ገይሩከ”

ትርጉም፡- “አላህ ሆይ! አንተን ከማመስገን ጋር አጠረሃለው፡፡ ስምህም ተባረከ፡፡ ክብርህም ከፍ አለ፡፡ ካንተ ሌላ በሐቅ የሚመለክ አምላክ የለም፡፡”

*ሱብሓነከ* ማለት ላንተ የሚገባውን ጥራት አጠረሃለው፣ *ወቢሐምዲከ* ማለት ዉዳሴ ያንተ ነው፣ *ወተባረከ ኢስሙከ* ማለት በረካ አንተን በማውሳት ይገኛል፣ *ወተዓላ ጀድዱከ* ማለት ክብርህ ከፍ አለ ሲሆን “*ወላ ኢላሀ ገይሩከ*” ማለት ደግሞ በሰማይም ሆነ በምድር ካንተ ውጭ በሐቅ የሚመለክ አምላክ የለም ማለት ነው፡፡ ቀጥሎም፡-

أعوذ بالله من الشيطان الرجيم

ከአላህ እዝነት ከተባረረው ሸይጣን በአላህ (ሱወ) እጠበቃለው፡፡

“አዑዙ” ማለት አላህ ሆይ! ወዳንተ እጠጋለው፤ ባንተ እጠበቃለውም ማለት ነው፡፡ *“አሸይጣን አር-ረጂም”* ከአላህ እዝነት የተባረረና የራቀ ሸይጣን በዱንያና በኣይማኖቴ ጉዳይ ውስጥ እንዳይጎዳኝ ባንተ እጠበቃለው ማለት ነው፡፡

## ሶስተኛው ማእዘን፡

ሱረት አልፋቲሓን ማንበብ ነው፡፡ እሱም በሁሉም ረከዓ ውስጥ ማእዘን ነው፡፡ ማስረጃውም የነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) ቃል ነው፡- "ፋቲሐት አልኪታቢን ያልቀራ ሰው ሰላት የለውም፡፡" እሷ የቁርኣን እናት ናት፡፡

بسم الله الرحمن الرحيم

*በአላህ ስም እጅግ በጣም ርኅሩህ በጣም አዛኝ በኾነው፡፡* ይህ ደግሞ በረከትና እርዳታን ፍለጋ ነው፡፡ "አልሐምዱ" ውዳሴ ነው፡፡ በዐረብኛ ህግ ‹አሊፍ› እና ‹ላም› ወይም "አል" ስለምታጠቃልል ምስጋናን ሁሉ ታጠቃልላለች፡፡ ሰው እራሱ ባልሰራው ነገር እንደ ውበት ባለው ነገር መወደሱ ሙገሳ እንጅ ምስጋና አይባልም፡፡ "ረብ አል-ዓለሚን" ‹ረብ› ማለት የሚመለከ ፈጣሪ፣ ስሳይ ሰጪ፣ ንጉስ፣ ተቆጣጣሪና ሁሉንም ፍጡር በፀጋው ተንከባካቢ እንደማለት ነው፡፡ ‹አል-ዓለሚን› ከአላህ ውጭ ያለው ሁሉ ዓለም ይባላል፡፡ አላህ የሁሉም ጌታ ነው፡፡ "አር-ረሕማን" ለሁሉም ፍጡራን የሚደርስ እዝነት ሲሆን "አር-ረሒም" ደግሞ ለምእምናን ብቻ የሆነች እዝነት ናት፡፡ ማስረጃውም የአላህ (ሱ.ወ) ቃል ነው፡-

﴿وَكَانَ بِٱلۡمُؤۡمِنِينَ رَحِيمًا﴾ [الأحزاب: ٤٣]

"ለአማኞችም በጣም አዛኝ ነው፡፡" *አል-አሕዛብ፡43*

﴿مَٰلِكِ يَوۡمِ ٱلدِّينِ﴾ [الفاتحة: ٤]

የፍርዱ ቀን ባለቤት፤ ቀኑ የምርመራና የምንዳ ቀን ነው፡፡ ሁሉም

ሰው በሰራው ስራ ይመነዳል፡፡ ጥሩ ከሰራ በጥሩ ይመነዳል መጥፎም ከሆነ በመጥፎ ይመነዳል፡፡ ማስረጃውም የአላህ (ሱ.ወ) ቃል ነው፡-

﴿وَمَآ أَدۡرَىٰكَ مَا يَوۡمُ ٱلدِّينِ ١٧ ثُمَّ مَآ أَدۡرَىٰكَ مَا يَوۡمُ ٱلدِّينِ ١٨ يَوۡمَ لَا تَمۡلِكُ نَفۡسٌ لِّنَفۡسٍ شَيۡـٔٗاۖ وَٱلۡأَمۡرُ يَوۡمَئِذٖ لِّلَّهِ﴾ [الإنفطار: ١٧ – ١٩]

"የፍርድ ቀን ምን እንደኾነ ምን አሳወቀህ? ከዚያም የፍርዱ ቀን ምን እንደኾነ ምን አሳወቀህ? (እርሱ) ማንኛይቱም ነፍስ ለሌላይቱ ነፍስ ምንም ማድረግን የማትችልበት ቀን ነው፡፡ ነገሩም ሁሉ በዚያ ቀን ለአላህ ብቻ ነው፡፡" *አል-ኢንፍጣር፡17-19*

ሌላ ማስረጃም የነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) ቃል ነው፡- "ብልህ ማለት የነፍሱን ስሜት ተቆጣጥሮ ከሞት በኋላ ላለው ጊዜ የሰራ ሰው ነው፡፡ ደካማ ደግሞ ነፍሱን ስሜቷን ያስከተሌና በአላህ ላይ ከንቱ ምኞትን የተመኘ ሰው ነው፡፡" ‹አንተን ብቻ እንገዛለን› ማለት ካንተ ውጭ አንገዛም ማለት ነው፡፡ ይህ በባርያና በጌታው መካከል ያለው ቃልኪዳን ነው፡፡ እሱም ባርያው አላህን ብቻ ለመገዛት የገባው ቃል ነው፡፡ ‹አንተን ብቻ እርዳታን እንጠይቃለን› ማለት ከአላህ ሌላ እርዳታ ላለ መጠየቅ ባርያው ለአላህ ቃል እየገባ ነው፡፡ ‹ቀጥተኛን መንገድ ምራን› ምራን ማለት አመላክተነንና በዚያ ላይ አፅናን ማለት ነው፡፡ መንገዱ ደግሞ እስላም ነው፡፡ የአላህ መልእክተኛ ናቸው ወይም ቁርኣን ነውም ተብሏል፡፡ ሁሉም ሀቅ ነው፡፡ ቀጥተኛ ማለት ጥሜት የሌለበት ማለት ነው፡፡ *"የእነዚያን በነርሱ ላይ በጎ የዋልክላቸውን መንገድ"* የሚለው አላህ ውለታውን የዋለላቸው ሰዎች መንገድ ነው፡፡ ማስረጃውም የአላህ (ሱ.ወ) ቃል ነው፡-

﴿وَمَن يُطِعِ ٱللَّهَ وَٱلرَّسُولَ فَأُوْلَٰٓئِكَ مَعَ ٱلَّذِينَ أَنۡعَمَ ٱللَّهُ عَلَيۡهِم مِّنَ ٱلنَّبِيِّـۧنَ وَٱلصِّدِّيقِينَ وَٱلشُّهَدَآءِ وَٱلصَّٰلِحِينَۚ وَحَسُنَ أُوْلَٰٓئِكَ رَفِيقٗا﴾ [النساء: ٦٩]

"አላህንና መልክተኛውን የሚታዘዝ ሰው እነዚያ ከእነዚያ አላህ በእነርሱ ላይ ከለገሳቸው ከነቢያት፣ ከጻድቃንም፣ ከሰማዕታትም፣ ከመልካሞቹ ጋር ይኾናሉ፡፡ የእነዚያም ጓደኝነት አማረ፡፡" *አን-ኒሳእ፡69*

*"ያልተቆጣህባቸውን ሰዎች መንገድ"* አላህ የተቆጣባቸው ሰዎች አይሁዶች ናቸው፡፡ እውቀት አላቸው፤ በእውቀታቸው አልሰሩም፡፡ አላህ ከመንገዳቸው እንዲያርቅህ እንለምነዋለን፡፡ *"ያልተሳሳቱትንም ሰዎች መንገድ"* የተሳሳቱ ሰዎች ነሳራዎች ናቸው፡፡ በመኃይምነት ላይ አላህን ይገዛሉ፡፡ አላህ ከመንገዳቸውም እንዲያርቅህ እንለምነዋለን፡፡ ማስረጃውም የአላህ (ሱ.ወ) ቃል ነው፡-

﴿قُلۡ هَلۡ نُنَبِّئُكُم بِٱلۡأَخۡسَرِينَ أَعۡمَٰلًا ١٠٣ ٱلَّذِينَ ضَلَّ سَعۡيُهُمۡ فِي ٱلۡحَيَوٰةِ ٱلدُّنۡيَا وَهُمۡ يَحۡسَبُونَ أَنَّهُمۡ يُحۡسِنُونَ صُنۡعًا﴾ [الكهف: ١٠٣-١٠٤]

"በሥራዎች በጣም ከሳሪዎቹን እንንገራችሁን?› በላቸው፡፡ እነዚያ እነሱ ሥራን የሚያሳምሩ የሚመስላቸው ሲሆኑ በቅርቢቱ ሕይወት ሥራቸው የጠፋባቸው ናቸው፡፡" *አልከህፍ፡103-104*

ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) እንዲህ ይላሉ፡- "ቀስት ቀስትን የሚከተለውን ያክል ከእናንተ በፊት የነበሩ ህዝቦችን ትከተላላችሁ፡፡ የአርጃኖ (ወከሎ) ጉድጋድ ቢገቡ እንኳ ትገባላችሁ፡፡" ‹የአላህ መልእክተኛ ሆይ! አይሁዶችና ነሳራዎች ናቸውን?› አሉ፡፡ ነቢዩም (ሰ.ዐ.ወ) "ታዲያ ማንን ነው!!" አሉ፡፡ ቡኻሪና ሙስሊም ዘግበውታል፡፡ በሌላ ሐዲስ ነቢዩ

(ሰ.ዐ.ወ) እንዲህ አሉ፡- "አይሁዶች በ 71 ጭፍራዎች ተከፋፈሉ፡፡ ነሳራዎች ደግሞ በ 72 ጭፍሮች ተከፋፈሉ፡፡ ይህች ኡማም ገና በ 73 ትከፋፈላለች፡፡"አንዷ ብቻ ሲትቀር ሁሉም የእሳት ናቸው፡፡" ‹የአላህ መልእክተኛ ሆይ! እሷ ማን ናት?› አልን፡፡ ነቢዩም (ሰ.ዐ.ወ) "እኔና ሰሓቦቼ ባለንበት መንገድ አምሳያ ላይ የተገኘ ሰው ነው" አሉ፡፡

## አራተኛው ማእዘን፡

ሩኩዕ ማድረግ (ማጎንበስ)፣

## አምስተኛው ማእዘን፡

ከሩኩዕ ቀጥ ብሎ መቆም፣

## ስድስተኛው ማእዘን፡

በሰባት አካላት ላይ ሱጁድ ማድረግ፣

## ሰባተኛው ማእዘን፡

ከሱጁዱ መነሳት፣

## ስምንተኛው ማእዘን፡

በሁለቱ ሱጁዶች መካከል መቀመጥ ነው፡፡ ማስረጃውም የአላህ (ሱ.ወ) ቃል ነው፡-

﴿يَٰٓأَيُّهَا ٱلَّذِينَ ءَامَنُواْ ٱرۡكَعُواْ وَٱسۡجُدُواْ﴾ [الحج: ٧٧]

"እናንተ ያመናችሁ ሰዎች ሆይ! (በስግደታችሁ) አጎንብሱ፣ በግንባራችሁም ተደፉ፡፡" *አልሐጅ፡77*

በሐዲስ ውስጥ ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) እንዲህ አሉ፡- “በሰባት አካላት ሱጁድ መውረድ ታዘዝኩኝ፡፡”

## ዘጠነኛው ማእዘን፡

በሁሉም የሰላት ስራዎች ዉስጥ መረጋጋት፣

## አስረኛው ማእዘን፡

በየማእዘናቱ መካከል ያለውን ቅደም ተከተል መጠበቅ ነው፡፡ ማስረጃውም ሰላቱን ያበላሸ ሰውዬ ሐዲስ ነው፡፡ አቡ ሁረይራ (ረዐ) እንዲህ ይላል፡- “አንዴ ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) ዘንድ ተቀምጠን እያለን አንድ ሰው ገባና ሰግዶ ለነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) ሰላምታ አላቸው፡፡ ነቢዩም (ሰ.ዐ.ወ) “ተመልሰህ ስገድ አልሰገድክምና” አሉት፡፡ ሶስት ጊዜ እንዲህ አደረገ፡፡ ሰውየውም ቀጥሎ እንዲህ አለ ‹በሐቅ በላከህ ጌታ ይሁንብኝ! ከዚህ በላይ ማሳመር አልችልም፤ ስለዚህም አስተምሩኝ፡፡› ነቢዩም (ሰ.ዐ.ወ) እንዲህ አሉት፡- “ለሰላት በተነሳህ ጊዜ ተክቢራ አድርግ፡፡ ከዚያም ከቁርአንም የቻልከውን ያህል ቅራ፡፡ ከዚያም በሩኩዕህ ላይ እስክትረጋጋ ድረስ ሩኩዕ አድርግ፡፡ ከዚያም ከሩኩዕ ተነስተህ እስከምትረጋጋ ድረስ ቀጥ ብለህ ቁም፡፡ ከዚያም በሱጁድ ላይ እስከምትረጋጋ ድረስ በመቀጠል ሱጁድ አድርግ፡፡ ከዚያም እስክትረጋጋ ድረስ ከሱጁድ ቀና በልና ተቀመጥ፡፡ ከዚያም በሱጁድ ላይ እስከምትረጋጋ ድረስ ሱጁድ አድርግ፡፡ ከዚያም በየሰላትህ ሁሉ እንዲሁ አድርግ፡፡”

## አስራ አንደኛ ማእዘን፡

የመጨረሻውን አት-ተሕያቱን መቅራት ነው፡፡ እሱም በሐዲስ እንደተጠቀሰው ግዴታ የሆነ ማእዘን ነው፡፡ ኢብን መስዑድ (ረዐ) እንዲህ ይላል፡- አት-ተሕያቱን መቅራት በኛ ላይ ግዴታ ከመደረጉ በፊት “ከባሮቹ የሆነ ሰላም በአላህ ላይ ይስፈን፤ ሰላም በጅብሪልና ሚካኢል ላይ ይስፈን” እንል ነበር፡፡ ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) እንዲህ አሉ፡- “ከባሮቹ የሆነ ሰላም በአላህ ላይ ይስፈን፣ አትበሉ፡፡ አላህ እራሱ ሰላም ነው፡፡ ነገር ግን (የሚቀጥለውን) በሉ፡-

التحيات لله، والصلوات، والطيبات، السلام عليك أيها النبي ورحمة الله وبركاته، السلام علينا وعلى عباد الله الصالحين، أشهد ألا إله إلا الله، وأشهد أن محمدا عبده ورسوله.

*“አት-ተሒያቱ ሊልላሂ፥ ወስ-ሶለዋቱ ወጥ-ጠይዪባቱ፡፡ አስ-ሰላሙ ዐለይከ አይዩሃን- ነቢዩ ወረሕመቱልላሂ ወበረካቱሁ፡፡ አስ-ሰላሙ ዐለይና ወዐላ ዒባዲልላሂ አስ-ሷሊሒን፡፡ አሽሀዱ አን ላ ኢላሀ ኢልለ-ልላህ ወአሽሀዱ አንነ ሙሐመደን ዐብዱሁ ወረሱሉሁ፡፡”*

ትርጉም፡- ክብሮች ሁሉ የአላህ ናቸው፤ ፀሎቶችና መልካም ነገሮችም፡፡ አንቱ ነቢይ ሆይ! ሰላም ባንቱ ላይ ይሁን፤ የአላህ እዝነትና በረከቱም፡፡ ሰላም በኛና በደጋግ የአላህ ባሮች ላይ ይሁን፡፡ ከአላህ ሌላ በሐቅ የሚመለክ አምላክ እንደ ሌለ እመሰክራለዉ፤ ሙሐመድም የአላህ ባርያና መልእክተኛው መሆናቸውን እመሰክራለዉ፡፡

“አት-ተሕያቱ” ማለት የሁሉም ክብር ባለቤትና ልከበር የሚገባውም አላህ ነው፡፡ ለምሳሌ ራስህን ዝቅ ማድረግ፣ ማጎንበስ፣ ሱጁድ

ማድረግ፣ ዘላቂነት እና ዘውታርነት የሚገባው ለአላህ ብቻ ነው፡፡ ከነዚህ ውስጥ አንዱን ለሌላ የሰጠ ሰው ሙሽሪክ ከሀዲ ይሆናል፡፡ "አስ-ሰለዋት" ደግሞ ፀሎቶችን ሁሉ ያካትታል፡፡ አምስቱ ሰላትም ነው ተብሏል፡፡ *"ወጥ-ጠይዪባቱ ሊላሂ"* አላህም ጥሩ ነው፡፡ ከንግግርና ድርጊት መልካምን እንጂ አይቀበልም፡፡ *"አንቱ ነቢይ ሆይ! ሰላም ባንቱ ላይ ይሁን፤ የአላህ እዝነትና በረከቱም"* በሚለው ለነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) ሰላም፣ እዝነትና በረከትን ትለምናለህ፡፡ የሚለመንላቸው ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) ከአላህ ጋር አይለመኑም፡፡ *"ሰላም በኛና በደጋግ የአላህ ባሮች ላይ ይሁን"* በሚለው ደግሞ ለራስህ፣ በሰማይና በምድር ውስጥ ላሉት ለአላህ ባሮች ሁሉ ሰላምን ትለምናለህ፡፡ *"አሽሀዱ አን ላ ኢላሀ ኢልለ-ልላሀ"* በምድርና በሰማይ ውስጥ ከአላህ ሌላ በሐቅ የሚመለክ አምላክ እንደሌለ እውነተኛ ምስክር ትመሰክራለህ፡፡ ሙሐመድ የአላህ መልእክተኛ ናቸው ብሎ መመስከር ደግሞ ባርያ ናቸው አይመለኩም፤ መልእክተኛ ናቸው አናስተባብላቸውም የሚለውን ያስይዛል፡፡ ይልቁንስ እንታዘዛቸዋለን፤ እንከተላቸዋለንም፡፡ አላህ በባርያነት አከበራቸው፡፡ ማስረጃውም የአላህ (ሱ.ወ) ቃል ነው፡-

﴿تَبَارَكَ ٱلَّذِى نَزَّلَ ٱلْفُرْقَانَ عَلَىٰ عَبْدِهِۦ لِيَكُونَ لِلْعَٰلَمِينَ نَذِيرًا﴾ [الفرقان: ١]

"ያ ፉርቃንን በባሪያው ላይ ለዓለማት አስፈራሪ ይኾን ዘንድ ያወረደው (አምላክ) ክብርና ጥራት ተገባው፡፡" *አልፉርቃን፡ 1*

## አስራ ሁለተኛው ማእዘን፡

ለተሸሁድ (አት-ተሕያቱ) መቀመጥ፣

## አስራ ሶስተኛ ማእዘን፡

ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) ላይ ሰላዋት ማውረድ ነው፡፡ እሱም፡-

اللهم صل على محمد، وعلى آل محمد، كما صليت على إبراهيم وعلى آل إبراهيم، إنك حميد مجيد، وبارك على محمد، وعلى آل محمد، كما باركت على إبراهيم، وعلى آل إبراهيم إنك حميد مجيد.

አላህ ሆይ! በኢብራሂምና በቤተሰቦቹ ላይ እዝነትን እንዳወረድክ ሁሉ በሙሐመድና በቤተሰቦቹ ላይ እዝነትህን አዉርድ፡፡ አንተ ምስጉንና የላቅክ ነህና፡፡ በኢብራሂምና በቤተሰቦቹ ላይ በረከት እንዳወረድከው ሁሉ በሙሐመድና በቤተሰቦቹ ላይ በረከት አዉርድ፤ አንተ ምስጉንና የላቅክ ነህና፡፡

አላህ ሰለዋት አደረገ የሚባለው ባርያውን በተከበሩት የላይኞቹ ጭፍሮች (መላእከት) ውስጥ ማወደስ ነው፡፡ ይህንን ቡኻሪ ሰሒሕ በሆነ ኪታባቸው ውስጥ ከአቢል ዓሊያ ዘግበውት እንዲህ አለ፡- “የአላህ ሰለዋት የሚባለው ባርያውን በተከበሩት የላይኞቹ ጭፍሮች (መላእከት) ውስጥ ማወደስ ነው፡፡” እዝነትም ነው Z ትክክለኛው ራዕይ የመጀመሪያው ነው፡፡ የመላእኮች ሰለዋት ምህረትን መጠየቅ ሲሆን የሰው ልጆች ደግሞ ዱዓእ ማድረግ ነው፡፡

## አስራ አራተኛው ማእዘን፡

በሁለቱም ጎን ማሰላመት ነው፡፡ “ወበረካቱሁ” እና ከሱ በኋላ ያለው ንግግርና ድርጊት ሁሉ ሱና ነው፡፡

## የሰላት ዋጅባቶች ስምንት ናቸው፡፡ እነሱም፡-

01 ከመጀመሪያ ተክቢራ ዉጭ ያሉ ሌሎች ተክቢራዎች፣

02 ሩኩዕ ዉስጥ ‹ሱብሓነ ረብየል ዐዚም› (ታላቁ ጌታዬ ላንተ ከማይገባህ ሁሉ ጥራት ይገባህ) ማለት፣

03 ለእማምና ብቻዉን ለሚሰግድ ሰው ‹ሰሚዐላሁ ሊመን ሐሚደህ› (አላህ እሱን ያመሰገኔን ሰው ሰምቷል) ማለት፣

04 ሁሉም ሰጋጅ ‹ረበና ወለከል ሐምዱ› (ጌታችን ሆይ! ምስጋና ያንተ ነው) ማለት፣

05 ሱጁድ ዉስጥ ‹ሱብሓነ ረብየል አዕላ› (የላቁ ጌታዬ ላንተ ከማይገባህ ሁሉ ጥራት ይገባህ) ማለት፣

06 በሁለቱ ሱጁዶች መካከል ‹ረብግፍርሊ› (ጌታዬ ሆይ! ማረኝ) ማለት፣

07 የመጀመሪያውን አት-ተሕያቱን መቅራት እና

08 ለሱም መቀመጥ ናቸው፡፡

ከማእዘናት መካከል በመርሳትም ሆነ ሆን ተብሎ የተተወ እሱን በመተው ሰላቱ ይበላሻል፡፡ ከዋጅባቶች ደግሞ ሆን ተብሎ የተተወ ከሆነ እሱን በመተው ሰላቱ ይበላሻል፡፡ በመርሳት ከሆነ ደግሞ “ሱጁድ አስ-ሰህው” ይጠግነዋል፡፡ አላህ ሁሉንም አዋቂ ነው፡፡ ተፈፀመ!!!



# አልቀዋዒድ አልአርበዐህ
# አራቱ መሰረታዊ መርሆዎች

የትልቁ ዙፋን ባለቤት የሆነውን ቸሩን አላህ በአዱንያና በአኺራ እንዲወድህ፣ ባለህበት ቦታ ሁሉ የተባረከ ሰው እንዲያደርግህ፣ የተሰጠ ግዜ አመስጋኝ፣ የተፈተነ ጊዜ ታጋሽና ባጠፋ ጊዜ ምህረት የሚጠይቅ እንዲያደርግህም እለምነዋለው፡፡ እነዚህ ሶስቱ የመጨረሻዎቹ የስኬት አይነቶች ናቸው፡፡ አላህ እሱን ለመታዘዝ ያቅናህና ትክክለኛው የኢብራሂም መንገድ የሚባለው ለአላህ ኅይማኖትን ጥርት አድርገህ እሱን ብቻ መገዛትህ መሆኑን እወቀው፡፡ ማስረጃውም የአላህ (ሱ.ወ) ቃል ነው፡-

﴿وَمَا خَلَقْتُ ٱلْجِنَّ وَٱلْإِنسَ إِلَّا لِيَعْبُدُونِ﴾ [الذاريات: ٥٦]

“ጋኔንንና ሰውንም ሊግገዙኝ እንጅ ለሌላ አልፈጠርኳቸውም፡፡” *አዝ-ዛርያት፡56*

አላህ (ሱወ) ለዒባዳው (እሱን ለመገዛት) እንደፈጠረን ካወቅክ፣ ሰላት ያለ ዉዱእ ሰላት እንደማይባል ሁሉ አምልኮትም ያለተውሒድ ዒባዳ እንደማይባል እወቅ፡፡ ሽንት ዉዱን እንደሚያጠፋ ሁሉ ሽርክ

ዒባዳ ውስጥ ከገባ ዒባዳውን ያበላሻል፡፡ ሽርክ ዒባዳ ጋር ከተቀላቀለ ዒባዳውን እንደሚያበላሽና ስራውን አጥፍተውበት ባለቤቱ እሳት ውስጥ ዘውታሪ መሆኑን ካወቅክ፣ ባንተ ላይ በጣም አሳሳቢ ጉዳይ የሚሆነው እሱን ማወቅ እንደሆነ ታውቀለህ፡፡ አላህ ከዚህ እውቀት ከዚህ መረብ ሊያጠራህ ይከጀላልና፡፡ እሷም በአላህ (ሱወ) ማጋራት ናት፡፡ አላህ ሽርክን አስመልክቶ እንዲህ ይላል፡-

﴿ إِنَّ ٱللَّهَ لَا يَغۡفِرُ أَن يُشۡرَكَ بِهِۦ وَيَغۡفِرُ مَا دُونَ ذَٰلِكَ لِمَن يَشَآءُ ﴾ [النساء: ١١٦]

"አላህ በርሱ የማጋራትን (ወንጀል) አይምርም፡፡ ከዚህም ወዲያ ያለውን ለሚሻው ሰው ይምራል፡፡" *አን-ኒሳእ፡116*

ይኸም አላህ በቁርአን ውስጥ የተናገራቸውን አራት መሰረታዊ መርሆዎችን በማወቅ ይሆናል፡፡ እነሱም፡-

## የመጀመሪያ መርህ፡

እነዚያ ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) የተጋደሏቸው ካፊሮች አላህ (ሱወ) ፈጣሪ፣ ሰሳይ ሰጪና ተቆጣጣሪ መሆኑን እንደሚያረጋግጡና ይህን ማረጋገጣቸው ኢስላም ውስጥ እንዳላስገባቸው ማወቅህ ነው፡፡ ማስረጃውም የአላህ (ሱ.ወ) ቃል ነው፡-

﴿ قُلۡ مَن يَرۡزُقُكُم مِّنَ ٱلسَّمَآءِ وَٱلۡأَرۡضِ أَمَّن يَمۡلِكُ ٱلسَّمۡعَ وَٱلۡأَبۡصَٰرَ وَمَن يُخۡرِجُ ٱلۡحَيَّ مِنَ ٱلۡمَيِّتِ وَيُخۡرِجُ ٱلۡمَيِّتَ مِنَ ٱلۡحَيِّ وَمَن يُدَبِّرُ ٱلۡأَمۡرَۚ فَسَيَقُولُونَ ٱللَّهُۚ فَقُلۡ أَفَلَا تَتَّقُونَ ﴾ [يونس: ٣١]

"ከሰማይና ከምድር ሲሳይን የሚሰጣችሁ ማን ነው? መስሚያዎችንና ማያዎችንስ የፈጠረ ማን ነው? ከሙትም ሕያውን የሚያወጣ ከሕያውም ሙትን የሚያወጣስ ማን ነው? ነገሩን ሁሉ የሚያስተናብርስ

ማን ነው?» በላቸው:: «በእርግጥም አላህ ነው» ይሉሃል:: «ታዲያ (ለምን ታጋራላችሁ?) አትፈሩትምን?» በላቸው::" *ዩኑስ:31*

## ሁለተኛው መርህ:

እነሱም (ካፊሮቹም) እንዲህ ይሉ ነበር "እኛ እነሱን የለመንና ወደነሱ የዞርንበት ምክንያት ወደአላህ መቃረብና ምልጃን ፍለጋ ብቻ ነው:: " መቃረብን ፍለጋ ለሚለው ማስረጃው የአላህ (ሱ.ወ) ቃል ነው:-

﴿وَٱلَّذِينَ ٱتَّخَذُواْ مِن دُونِهِۦٓ أَوۡلِيَآءَ مَا نَعۡبُدُهُمۡ إِلَّا لِيُقَرِّبُونَآ إِلَى ٱللَّهِ زُلۡفَىٰٓ إِنَّ ٱللَّهَ يَحۡكُمُ بَيۡنَهُمۡ فِي مَا هُمۡ فِيهِ يَخۡتَلِفُونَۗ إِنَّ ٱللَّهَ لَا يَهۡدِي مَنۡ هُوَ كَٰذِبٞ كَفَّارٞ﴾

[الزمر: ٣]

"እነዚያም ከእርሱ ሌላ (ጣዖታትን) ረዳቶች የያዙት «ወደ አላህ ማቃረብን እንዲያቀርቡን እንጅ ለሌላ አንገዛቸውም» (ይላሉ):: አላህ በዚያ እነርሱ በእርሱ በሚለያዩበት ነገር በመካከላቸው ይፈርዳል:: አላህ እርሱ ውሸታም ከሓዲ የኾነን ሰው አያቀናም::" *አዝ-ዙመር:3*

የምልጃ ማስረጃም የአላህ (ሱ.ወ) ቃል ነው:-

﴿وَيَعۡبُدُونَ مِن دُونِ ٱللَّهِ مَا لَا يَضُرُّهُمۡ وَلَا يَنفَعُهُمۡ وَيَقُولُونَ هَٰٓؤُلَآءِ شُفَعَٰٓؤُنَا عِندَ ٱللَّهِ﴾ [يونس: ١٨]

"ከአላህም ሌላ የማይጎዳቸውን የማይጠቅማቸውንም ይግገዛሉ:: «እነዚህም አላህ ዘንድ አማላጆቻችን ናቸው» ይላሉ:: «አላህን በሰማያትና በምድር ውስጥ የማያውቀው ነገር ኖሮ ትነግሩታላችሁን?» በላቸው:: ከሚያጋሩት ሁሉ ጠራ፤ ላቀም::" *ዩኑስ:18*

ምልጃ (ሸፋዓ) በሁለት ይከፈላል፡፡ እነሱም የተከለከለ ሸፋዓና የተፈቀደ ሸፋዓ ናቸው፡፡ የተከለከለ ሸፋዓ የሚባለው አላህ ብቻ የሚችለውን ነገር ከአላህ ሌላ ካለው አካል የሚፈለግ ሲሆን ማስረጃውም የአላህ (ሱ.ወ) ቃል ነው፡-

﴿ يَٰٓأَيُّهَا ٱلَّذِينَ ءَامَنُوٓاْ أَنفِقُواْ مِمَّا رَزَقۡنَٰكُم مِّن قَبۡلِ أَن يَأۡتِيَ يَوۡمٞ لَّا بَيۡعٞ فِيهِ وَلَا خُلَّةٞ وَلَا شَفَٰعَةٞۗ وَٱلۡكَٰفِرُونَ هُمُ ٱلظَّٰلِمُونَ ﴾ [البقرة: ٢٥٤]

"እናንተ ያመናችሁ ሆይ! በርሱ ውስጥ ሽያጭ (መበዦት)፣ ወዳጅነትም፣ ምልጃም የሌለበት ቀን ከመምጣቱ በፊት ከሰጠናችሁ ነገር ለግሱ፡፡ ከሓዲዎችም በዳዮቹ እነርሱ ናቸው፡፡" *አልበቀራ፡254*

የተፈቀደ ሸፋዓ የሚባለው ከአላህ (ሱወ) የሚፈለገው ሲሆን አማላጁው በምልጃው ይከበራል፡፡ ምልጃ የሚደረግለት ደግሞ አላህ ንግግሩንና ስራውን የወደደለት ሰው ብቻ ነው፡፡ እሱም ከአላህ ፈቃድ በኋላ ነው፡፡ አላህ (ሱወ) እንዲህ ይላል፡-

﴿مَن ذَا ٱلَّذِي يَشۡفَعُ عِندَهُۥٓ إِلَّا بِإِذۡنِهِۦ ﴾ [البقرة: ٢٥٥]

"ያ እርሱ ዘንድ በፈቃዱ ቢኾን እንጅ የሚያማልድ ማነው?" *አልበቀራ፡255*

## ሶስተኛ መርህ፡

ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) የተላያዩ ነገር በሚገዙ ሰዎች ላይ መጡ፡፡ ከነሱ ውስጥ መለይካዎችን የሚገዙ አሉ፡፡ ከነሱ መካከል ነቢያቶችንና ደጋግ ሰዎችን የሚገዙትም ነበሩ፡፡ እንዲሁም ዛፎችንና ድንጋዎችን የሚያመልኩም ነበሩ፡፡ ፀሓይንና ጨረቃን የሚገዙም እንዲሁ ነበሩ፡፡

ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) እነሱን ሳይለያዩዋቸው ተጋደሏቸው፡፡ ማስረጃውም የአላህ (ሱ.ወ) ቃል ነው፡-

﴿ وَقَٰتِلُوهُمۡ حَتَّىٰ لَا تَكُونَ فِتۡنَةٞ وَيَكُونَ ٱلدِّينُ كُلُّهُۥ لِلَّهِۚ ﴾ [الأنفال: ٣٩]

“ሁከትም እስከማትገኝ ሃይማኖትም ሁሉ ለአላህ ብቻ እስከሚኾን ድረስ ተጋደሏቸው፡፡” *አል-አንፋል፡39*

ፀሓይንና ጨረቃን የሚገዙ ሰዎች እንደነበሩ ማስረጃው የአላህ (ሱ.ወ) ቃል ነው፡-

﴿ وَمِنۡ ءَايَٰتِهِ ٱلَّيۡلُ وَٱلنَّهَارُ وَٱلشَّمۡسُ وَٱلۡقَمَرُۚ لَا تَسۡجُدُواْ لِلشَّمۡسِ وَلَا لِلۡقَمَرِ وَٱسۡجُدُواْۤ لِلَّهِ ٱلَّذِي خَلَقَهُنَّ إِن كُنتُمۡ إِيَّاهُ تَعۡبُدُونَ ﴾ [فصلت: ٣٧]

“ሌሊትና ቀንም ፀሐይና ጨረቃም ከምልክቶቹ ናቸው፡፡ ለፀሐይና ለጨረቃ አትስገዱ፡፡ ለእዚያም ለፈጠራቸው አላህ ስገዱ፡፡ እርሱን ብቻ የምትግገዙ እንደ ኾናችሁ (ለሌላ አትስገዱ)፡፡” *ፉስለት፡37*

የመላእክትም ማስረጃ የአላህ (ሱ.ወ) ቃል ነው፡-

﴿ وَلَا يَأۡمُرَكُمۡ أَن تَتَّخِذُواْ ٱلۡمَلَٰٓئِكَةَ وَٱلنَّبِيِّـۧنَ أَرۡبَابًاۗ ﴾ [آل عمران: ٨٠]

“መላእክትንና ነቢያትንም አማልክቶች አድርጋችሁ እንድትይዙ ሊያዛችሁ (አይገባውም)፡፡” *ኣሊ ዒምራን፡80*

የነቢያቶችም ማስረጃ የአላህ (ሱ.ወ) ቃል ነው፡-

﴿وَإِذۡ قَالَ ٱللَّهُ يَٰعِيسَى ٱبۡنَ مَرۡيَمَ ءَأَنتَ قُلۡتَ لِلنَّاسِ ٱتَّخِذُونِي وَأُمِّيَ إِلَٰهَيۡنِ مِن دُونِ ٱللَّهِۖ قَالَ سُبۡحَٰنَكَ مَا يَكُونُ لِيٓ أَنۡ أَقُولَ مَا لَيۡسَ لِي بِحَقٍّۚ إِن كُنتُ قُلۡتُهُۥ فَقَدۡ عَلِمۡتَهُۥۚ تَعۡلَمُ مَا فِي نَفۡسِي وَلَآ أَعۡلَمُ مَا فِي نَفۡسِكَۚ إِنَّكَ أَنتَ عَلَّٰمُ ٱلۡغُيُوبِ ﴾ [المائدة: ١١٦]

“አላህም፡- «የመርየም ልጅ ዒሳ ሆይ! አንተ ለሰዎቹ፡- እኔንና እናቴን ከአላህ ሌላ ሁለት አምላኮች አድርጋችሁ ያዙ ብላሃልን?» በሚለው ጊዜ (አስታውስ)፡፡ «ጥራት ይገባህ፤ ለእኔ ተገቢዬ ያልኾነን ነገር ማለት ለኔ አይገባኝም፡፡ ብዬው እንደ ኾነም በእርግጥ ዐውቀኸዋል፡፡ በነፍሴ ውስጥ ያለውን ሁሉ ታውቃለህ፡፡ ግን በነፍስህ ውስጥ ያለውን አላውቅም፡፡ አንተ ሩቆችን ሁሉ በጣም ዐዋቂ አንተ ብቻ ነህና» ይላል፡፡” *አልማኢዳ፡116*

የደጋግ ሰዎች ማስረጃ የአላህ (ሱ.ወ) ቃል ነው፡-

﴿ أُولَٰئِكَ الَّذِينَ يَدْعُونَ يَبْتَغُونَ إِلَىٰ رَبِّهِمُ الْوَسِيلَةَ أَيُّهُمْ أَقْرَبُ وَيَرْجُونَ رَحْمَتَهُ وَيَخَافُونَ عَذَابَهُ ۚ إِنَّ عَذَابَ رَبِّكَ كَانَ مَحْذُورًا ﴾ [الإسراء: ٥٧]

“እነዚያ እነርሱ የሚግገዟቸው ማንኛቸውም (ወደ አላህ) በጣም ቀራቢያቸው ወደ ጌታቸው መቃረቢያን (ሥራ) ይፈልጋሉ፡፡ እዝነቱንም ይከጅላሉ፡፡ ቅጣቱንም ይፈራሉ፡፡” *አል-ኢስራእ፡57*

የዛፎችና የድንጋይዎች ማስረጃ የአላህ (ሱ.ወ) ቃል ነው፡-

﴿ أَفَرَأَيْتُمُ اللَّاتَ وَالْعُزَّىٰ ﴿١٩﴾ وَمَنَاةَ الثَّالِثَةَ الْأُخْرَىٰ ﴾ [النجم: ١٩ – ٢٠]

“አል-ላትንና አል-ዑዛን አያችሁን? ሦስተኛይቱንም አነስተኛዋን መናትን (አያችሁን? የምትግገዟቸው ኃይል አላቸውን?)” *አን-ነጅም፡19-20*

በሐዲስ ውስጥ ከአቢ ዋቅድ አል-ለይሲ (ረዐ) ተዘግበው እንዲህ ይላል፡- “እኛ ጊዜያችን ወደ ኩፍር ቅርብ ሆኖ ሳለ ከነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) ጋር ወደ ሑነይን ወጣን፡፡ ሙሽርኮች ለአምልኮት እሷ ዘንድ የሚቀመጡና (በረከትን ፍለጋ) መሳሪያቸውን የሚያንጠለጥሉባት ቁርቁራ ነበረቻቸው፡፡ እሷም

የማንጠልጠሊያ ባለቤት ትባላለች፡፡ እኛም "አንቱ የአላህ መልእክተኛ ሆይ! እነሱ ማንጠልጠሊያ እንዳላቸው ሁሉ ለኛም ማንጠልጠሊያ አድርጉልን" አልን፡፡..."

## አራተኛ መርህ፡

የዘመናችን ሙሽርኮች ሽርካቸው ከቀደምቶች ይበልጣል፡፡ ምክንያቱም ቀደምቶች በተድላ ጊዜ ያጋራሉ፤ በችግር ጊዜ ደግሞ አምልኮትን ለአላህ ጥርት ያደርጋሉ፡፡ የዘመናችን ሙሽርኮች ደግሞ ሽርካቸው በተድላም ሆነ በችግር ጊዜ ቋሚ ነው፡፡ ማስረጃውም የአላህ (ሱ.ወ) ቃል ነው፡-

﴿ فَإِذَا رَكِبُوا۟ فِى ٱلْفُلْكِ دَعَوُا۟ ٱللَّهَ مُخْلِصِينَ لَهُ ٱلدِّينَ فَلَمَّا نَجَّىٰهُمْ إِلَى ٱلْبَرِّ إِذَا هُمْ يُشْرِكُونَ ﴾ [العنكبوت: ٦٥]

"በመርከቦች ውስጥ በተሳፈሩ ጊዜም አላህን መገዛትን ለእርሱ ብቻ ያጠሩ ኾነው ይጠሩታል፡፡ ወደ የብስ (በማውጣት) ባዳናቸው ጊዜም ወዲያውኑ እነርሱ (ጣዖትን) ያጋራሉ፡፡" *አል-ዐንከቡት፡65*

ተፈፀመ!!!

የአላህ እዝነትና ሰላም በሙሐመድ፣ በቤተሰቦቻቸውና በባልደረቦቻቸው ላይ ስፈን፡፡

IslamHouse.com
IslamHouseAM/ Bengali.IslamHouse islamhouse.com/am/
channel/UC0T_q-4JkqIMTfmxa1L3kTw

For more details visit
www.GuideToIslam.com
GUIDE TO ISLAM

contact us :Books@guidetoislam.com
Guidetolslam.org Guidetoislam1 Guidetoislam www.Guidetoislam.com

المكتب التعاوني للدعوة وتوعية الجاليات بالربوة
هاتف: ٠٠٩٦٦١١٤٤٥٤٩٠٠+ فاكس: ١٢٦٠٩٦٦١١٤٩٧٠+ ص ب: ٢٩٤٦٥ الرياض: ١١٤٥٧
ISLAMIC PROPAGATION OFFICE IN RABWAH
P.O.BOX 29465 RIYADH 11457 TEL: +966 11 4454900 FAX: +966 11 4970126

# አል-ኡሱል አስ-ሰላሰህ

# ሶስቱ መሰረታዊ መርሆዎች

ዐቂደህ በኢስላም ውስጥ ከፍተኛ ቦታ ያለው ጉዳይ ነው፣ ይህ መጽሃፍ ሶስቱ መሰረቶች ትምህርት በውስጡ ይዟዋል፣ አንብበው ዕውቀት እንድቀስሙ ተስፋ እናደርጋለን።




IslamHouse.com
OsoulCenter
www.osoulcenter.com